ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ 84 ዓመት ቁጥር 054 ጥቅምት 24 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# በብሪክስ ማሕቀፍ ውስጥ የኢትዮጵያ ተጠቃሚነት

**ሞገስ ጸጋዬ**

በሩሲያ ካዛን 16ኛው የብሪክስ ጉባዔ ላይ ሰፋ ያሉ ጉዳዮች ተዳሰውበታል፡፡ ኢትዮጵያም ተጠቃሚነቷን ለማስፋት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተመራ ልኡካን ተወክላም ነበር፡፡ ባለፈው ዓመት በተካሄደው ጉባዔ ኢትዮጵያን ጨምሮ ስድስት ሀገራት ብሪክስን መቀላቀላቸው ይታወሳል፡፡ ብሪክስ ኢትዮጵያን ጨምሮ 11 የሚደርሱ የሀገራት ስብስብ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የዓለማችን 45 በመቶ የሕዝብ ብዛት እና 35 በመቶ የዓለምን ኢኮኖሚ የያዙ ሀገራትን አሰባስቧል፡፡ ብሪክስ በተለያዩ የትኩረት መስኮች ላይ ትብብር የሚያደርግና የጋራ አቋም የሚያዝበት በመሆኑ ኢትዮጵያ የዚህ አባል መሆኗ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ አይነተኛ መንገድ ከፍቶላታል፡፡

“በብሪክስ ማዕቀፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ጌድዮን ጢሞትዮስ (ዶ/ር)



አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን

# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ዛሬ ይጀምራል

## - በአማራ ክልል የአስተባባሪዎች ሥልጠና በቀጣይ ሳምንት ይሰጣል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ቦንጋ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከሁለት ሺ 200 በላይ ተወካዮች የሚሳተፉበት አጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ በዛሬው እለት እንደሚጀመር የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ። በአማራ ክልልም የአስተባባሪዎች ሥልጠና በቀጣይ ሳምንት እንደሚሰጥ ተመልክቷል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር ሙሉጌታ አጎ እንደገለፁት፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30 በቦንጋ ከተማ በሚከናወነው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ፤ በክልሉ ከሚገኙ 57 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮችን የሚወክሉ ከሁለት ሺ 200 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይሳተፋሉ።

በክልል ደረጃ በሚካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ በጥልቀት በመመካከር አጀንዳዎችን የማሰባሰብና በሀገራዊ ምክክር የሚሳተፉ ተወካዮች መረጣ እንደሚካሄድ ገልጸዋል።

እንደ ኮሚሽነር ሙሉጌታ ገለፃ፤ በምክክር ሂደቱ ቁልፍ ከሆኑ ተግባራት መካከል አጀንዳን አካታችና አሳታፊ በሆነ ሂደት የማሰባሰብ እንዲሁም በሀገራዊ ምክክር ጉባዔው ላይ የሚሳተፉ ተወካዮችን የማስመረጥ ተግባር ነው፡፡

በሚካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍም ሀገር

በበጋ የስንዴ መስኖ 172 ሚሊዮን... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# በበጋ የስንዴ መስኖ 172 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በ2017 ዓ.ም በሁሉም ክልሎች የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በማልማት 172 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግኑኝነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤2017 ዓ.ም በሁሉም ክልሎች የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በማልማት 172 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

በ2017 ዓ.ም የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በአራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ በማልማት 172 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ሰፊ እንቅስቃሴ

በበጋ የስንዴ መስኖ 172 ሚሊዮን... ወደ ገጽ 11 ዞሯል















## በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከ34 ሺህ ቶን በላይ ቡና ወደ ማእከላዊ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው

ገጽ 2



ዜና

# በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከ34 ሺህ ቶን በላይ ቡና ወደ ማእከላዊ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ በጀት ዓመት ከ34 ሺህ ቶን በላይ ቡና ወደ ማእከላዊ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይለማሪያም ተስፋዬ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ባሳለፍነው በጀት ዓመት 24 ሺህ ቶን ቡና ከክልሉ ወደ ማዕከላዊ ገበያ የተላከ ሲሆን በ2017 ዓ.ም ይህንን ከፍ በማድረግ 34 ሺህ ቶን ቡና ወደ ማእከላዊ ገበያ ለማቅረብ እየሠራን ነው።

የቡና ምርታማነት በሄክታር ሰባት ነጥብ አራት ኩንታል ከነበረበት በ2017 ዓ.ም ስምንት ነጥብ ስምንት ኩንታል በሄክታር እንደሚገኝ የቅድመ ምርት ግምት መረጃ ያሳያል ያሉት አቶ ኃይለማርያም፤ በክልሉ 229 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ ቡና እንደሚለማ ገልጸዋል።

የቡና ማሣ ምርታማነት ግብ ለማሳካት ያረጁ ቡናዎችን በጉንደላና ነቅሎ በአዲስ በመተካት፣ የአረምና የኩትኳቶ ሥራ፣ ኮምፖስት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ የተሠሩ ሥራዎች ውጤት እያስገኙ መሆኑን ገልጸው፤ አሁን የአፈር ለምነትን የሚያሻሽሉና ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኙ ተስማሚ ደባል ሰብሎች ማልማት ላይ ትኩረት እንደተረገ ተናግረዋል።

በ2017 በጀት ዓመት ወደ ሥራ ይገባል ተብሎ ከታቀደው



**አቶ ኃይለማሪያም ተስፋዬ**

287 የታጠበ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሁለት መቶ የሚሆኑት ቅድመ ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል ያሉት አቶ ኃይለማርያም፤ 44 ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ወደ ሥራ መግባታቸውን ጠቁመዋል።

የእሸት ቡና አሰባሰብ የተጀመረባቸው አካባቢዎችን የግብይት ሥርዓት እና የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸው 25 ሺህ ቶን እሸት ቡና መለቀሙን ጠቅሰዋል፡፡

አክለውም፤ የቡና አሰባሰብ ሂደቱ ከአምና በተሻለ መልኩ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሰበሰብና የግብይት ሥርዓት የሚከናወን መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህም ተፈጻሚነት የሁሉም ማህበረሰብና ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጠይቀዋል።



**አቶ ደምሰው በንቲ**

## በጂቡቲ ወደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ከአንድ ሚሊዮን 857 ሺህ ቶን በላይ ዕቃ ገብቷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሶስት ወራት በጂቡቲ ወደብ በኩል ከአንድ ሚሊዮን 857ሺ 198 ቶን በላይ የተለያየ ዕቃ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አስታወቀ፡፡

ኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ ደምሰው በንቲ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ የንግድ እንቅስቃሴ የሚከናወንባቸው የተለያዩ የንግድ መስመሮ ቢኖሩም አብዛኛውን የወጪና ገቢ ንግድ ዋና በር ሆኖ እያገለገለ የሚገኘው የጂቡቲ ወደብ ነው፡፡

ባለፉት ሶስት ወራትም በጂቡቲ ወደብ በኩል አንድ ሚሊዮን 857 ሺ 198 ቶን በኮንቴይነርና ከኮንቴይነር ውጪ ያለ ደረቅ ጭነት ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን ተናግረዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ ከጂቡቲ ውጪ በኬንያ ላሙ ወደብ በኩል 60ሺ107 ቶን ማዳበሪያ ተጓጓዘ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 13ሺ 246 ቶን የሚሆነው ወደ ሞያሌ ተጓጉዟል ብለዋል፡፡ ይህም ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን አጠቃላይ ጭነት መጠን ወደ አንድ ሚሊዮን 870 ሺ 444 ቶን ከፍ እንዲል ማድረጉን አብራርተዋል፡፡

አቶ ደምሰው፤ በሩብ ዓመቱ በኢባትሎ በባሕር የተጓጓዘ ጠቅላላ ደረቅ ጭነት 669ሺ 400 ቶን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 267ሺ 300 ቶን የሚሆነው ከኮንቴይነር ውጪ ቀሪው 402 ሺ 100 ቶን ደግሞ በኮንቴይነር የታሸገ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ዳይሬክተሩ ድርጅቱ በሺፒንግ አገልግሎት ዘርፍ፣ በጭነት አስተላላፊነት አገልግሎት ዘርፍ፣ በወደብና ተርሚናል ዘርፍ የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠቱን ጠቅሰው፤ ለአብነትም በሺፒንግ አገልግሎት ዘርፍ የድርጅቱን መርከቦችንና የኪራይ መርከቦችን በመጠቀም 860ሺ 387 ቶን እቃ መጓጓዙን ገልጸዋል፡፡

ይህም አፈጻጸሙ ከ2016 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተጓጓዘው አንድ ሚሊዮን 194ሺ 451 ቶን ጭነት ጋር ሲነፃፀር በ28 በመቶ ዝቅ ያለ መሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

ተቋሙ በሩብ ዓመቱ ከሚሰጡ አገልግሎቶችና ከሌሎች የገቢ ምንጮች 20 ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ 21 ነጥን ሁለት ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን የገለጹ ሲሆን፣ 18 ነጥብ 79 ቢሊዮን ብር ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ወጪ አድርጓል፡፡ በዚህም በሩብ ዓመቱ ሁለት ነጥብ 41 ቢሊዮን ብር ከታክስ በፊት ትርፍ ማግኘቱን አስረድተዋል፡፡

ይህም ከ2016 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ገቢ በ62 ነጥብ አራት በመቶ ፤ ወጪ በ69 በመቶ ፤ ትርፍ በ24 ነጥብ አራት በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን አቶ ደምሰው አብራርተዋል፡፡

## ኮርፖሬሽኑ በሩብ ዓመት ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት መሳብ መቻሉ ተገለፀ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያ ሶስት ወራት ውስጥ ከ300 ሚሊዮን በላይ የአሜሪካን ዶላር ያስመዘገቡ ኢንቨስተሮች መሳቡን ገለፀ፡፡ ኮርፖሬሽኑ በሚያስተዳድራቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮችና የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና 45 ባለሀብቶች መሳብ መቻሉ አስታውቋል፡፡

የኮርፖሬሽኑ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዘመን ጁነዲ እንደገለጹት፤ ባለፉት ሶስት ወራት ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የተለያዩ ሼዶችና የለማ መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ኢንቨስት ካደረጉት ባለሀብቶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት አቅም ያላቸው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሲሆኑ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ እንደተሠማሩ ገልፀው፤ ይህም ከዕቅዱ አንፃር ከፍተኛ መሆኑን ተጠቅሷል፡፡

በተጨማሪም የቻይና ፤ የጃፓንና የቬትናም ባለሀብቶችም ከተሳቡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ውስጥ እንደሚገኙበት ተገልጿል። በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ኢንቨስት ያደረጉት ባለሀብቶች ሃዋሳ፤ ኮምቦልቻ፤ ቦሌ ለሚ እና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ገብተው የሚሠሩ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ለአፈፃፀሙ ከፍተኛ መሆን ባለፉት ዓመታት መንግሥት የኢንቨስትመንት ከባቢውን ምቹ ለማድረግ የወሳደቻው ማበረታቻዎች ፤ ለሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶች የተሰጠው ትኩረት ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ያሉ ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮችና የኮርፖሬሽኑ አገልግሎት አሰጣጥ እየተሻሻለ መምጣት ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው በሪፖርቱ ላይ ተመላክተዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሶስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የግምገማ መድረክ የኮርፖሬሽኑ የማኔጅመንት አባላት እና የመምሪያ ኃላፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል፡፡



**አቶ ዘመን ጁነዲ**

## በክልሉ በሩብ ዓመቱ ለ170 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ተሰጥቷል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሩብ ዓመቱ ለ170 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠቱን የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ገለጸ፡፡ በክልሉ ኢንቨስት ያደረጉ ባለሀብቶች ካፒታላቸው 43 ቢሊዮን ብር መድረሱንም አስታውቋል፡፡

የቢሮ ኃላፊ ኦንጋዬ ኦዳ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ሶስት ወራት ውስጥ 200 የሚሆኑ የኢንቨስመንት ፍቃድ ጥያቄዎች ለክልሉ ቀርበው ግምገማ ተደርጎባቸው 170 ለሚሆኑት የኢንቨስትመንት ፍቃድ ተሰጥቷል፡፡

ባለፈው ዓመትም ከቀረበው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ 120 ለሚሆኑ ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ መሰጠቱንም ተናግረዋል፡፡

እስከአሁን ድረስ በክልሉ ኢንቨስት ያደረጉ ባለሀብቶች ካፒታላቸው 43 ቢሊዮን ብር መድረሱን ገልጸው፤ በክልሉ በሶስቱ በአገልግሎት፣ በግብርና እና በኢንዱስትሪ ዘርፎች የኢንቨስትመንት ሥራዎች እንደሚከናወኑ ጠቁመዋል፡፡ በክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፉ በቋሚ 30ሺ 400 ለሚሆኑ ዜጎች እንዲሁም በጊዜያዊነት 94ሺ 600 የለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩንም ተናግረዋል፡፡



**ኦንጋዬ ኦዳ(ዶ/ር)**

ወደ ክልሉ ለሚመጡ ባለሀብቶች ምቹ ለማድረግ አሠራሮችን በማሻሻል የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ከዞን በቀጥታ ወደ ኢንቨስትመንት ቢሮ እንዲመጣ መደረጉን ጠቁመው፤ ቢሮው ሥራውን ዲጂታይዝ በማድረግ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ጥያቄዎች በአብዛኛው በዲጂታል መንገድ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ እቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የአንድ ማዕከል አገልግሎትንም ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል፡፡

ኢንቨስትመንት ድጋፍ እና ክትትል እንደሚፈልግ የተናገሩት ቢሮ ኃላፊው፤ በድጋፍ እና ክትትል ሥራ ወደ ባለሀብቶቹ በመቅረብ ያሉ ችግሮችን በመለየት እገዛ እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡ በባለሀብቶቹ በኩል ሃላፊነትን ያለመወጣት ችግር ካለ በመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እስከ መሬት መንጠቅ የሚደርሱ ቅጣቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ አመልክተዋል፡፡ አሁን ላይ ለረዥም ዓመታት መሬት ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ የተወሰኑ ባለሀብቶች ላይ መሬት የመቀነስ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ሲመጡ የኢንቨስትመንት መሬት ተዘጋጅቶ እንደሚጠብቃቸው ጠቅሰው፤ ዞኖች ለኢንቨስትመንት የሚሆኑ 100 ሺ ሄክታር መሬት ማዘጋጀታቸውንም ጠቁመዋል፡፡

ክልሉ በተፈጥሮ ሀብት የታደለ፣ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ የሚዘንብበት እና ሰላማዊ ክልል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች ወደ ክልሉ መጥተው ቢያለሙ ራሳቸውንና ሀገራቸውን የሚጠቅሙ በመሆኑ በክልሉ እንዲያለሙ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

## በኢንዱስትሪ ፓርኩ የተመረተ 22 ቶን የአቮካዶ ዘይት ለውጭ ገበያ ቀርቧል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የዲላ መካከለኛ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመረተውን 22 ቶን የአቮካዶ ዘይት ለውጭ ገበያ ማቅረቡን አስታወቀ፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጥላሁን ብርሃኑ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ወደ ሥራ ከገባ በኋላ በሀገር በቀል አልሚ ድርጅት እየተመራ የተቀናጀ የግብርና ምርት እና የኦፕሬሽን ሥራ እያከናወነ ይገኛል፡፡ በፓርኩም 22 ቶን የአቮካዶ ዘይት ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል፡፡

ኢንዱስትሪ ፓርኩ በአሁኑ ሰዓት በአንድ ሽፍት (ለስምንት ሰዓታት) የሚሠራ ሲሆን፤ለመጀመሪያ ጊዜ

**በኢንዱስትሪ ፓርኩ.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰው ተኮር የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ወደላቀ ደረጃ የማሸጋገር ኃላፊነት

ሀገር በሰው፤ ሰውም በሀገር የመኖርና የመጽናታቸው ምስጢር የገባቸው ጥቂት ሀገራትና መንግሥታት የሀገራዊ የልማት ሥራዎቻቸውን ሰውን ማዕከል አድርገው ይከውናሉ፡፡ ይሄ ያልገባቸው ደግሞ የልማት ሥራዎቻቸው ሁሉ ሰውን የገፉ፤ ሰውን ያላማከሉ፤ ውበትና ድምቀት እንጂ ሠብዓዊነትን ያልተላበሱ ይሆናሉ፡፡ እናም ሰው እና ልማት ማዶ ለማዶ ሆነው ልማቱ ሰውን ሳያውቅ፤ ሰውም ከልማቱ ሳይገናኝ ይኖራሉ፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በዘመናት ውስጥ በሁለቱም መልክ ተገልጣለች፡፡ ለምሳሌ፣ ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ቀደም ብለው የነበሩ ሦስት አስርት ዓመታትን እና ከለውጡ ማግስት ያሉ ስድስት ዓመታትን ለማንጻሪያነት እናንሳ፡፡ ከለውጡ በፊት ያሉ ዓመታት፣ እንደ ሀገር ተከታታይ የሚባል ልማት እና የኢኮኖሚ እድገት (ያውም ባለ ሁለት አሃዝ እድገት የተባለለት ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት) አስመዝግባለች፡፡

ይሄ እድገት ግን አንድም የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል፣ ሁለተኛም የዜጎችን የስራ ዕድል ፈጠራና ተጠቃሚነት እውን በማድረግ፤ ሦስተኛም ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ በኩል ይሄ ነው የሚባል ረብ አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም፣ ልማትና ሰው ሳይገናኙ፤ ልማቱ ሰው እንዳሳደደ፣ ሰውም ከልማቱ እንዲሸሽ እንደተደረገ የኖረበት ነበርና፡፡

ለዚህም ነው ሰው ልማትን መመልከት ሳይሆን፣ ከልማት የመጠቀም ከፍ ያለ መሻቱ፤ ፍትሃዊ እና የእኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት ፍላጎቱ፤ የልማት ሥራዎቹ የዜጋውን ማኅበራዊ ስሪት፣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት፣ ሥነልቦናዊ ማንነትና ልዕልና በሚያጎናጽፈው መልኩ እንዲሆንለት ከፍ ያለ ህልምን በመሰነቅ ሀገራዊ ለውጡ እንዲመጣ ከፍ ባለ ሕዝባዊ ተቃውሞ የለውጡ አንድ አቅምና ገፊ ምክንያት ሆኖ ለውጡን ያዋለደው፡፡

ከለውጥ በኋላ የተሠሩ ሥራዎች እና አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች ታዲያ፤ ይሄንን የለውጥ አዋላጅ የሆነ ሕዝብ ፍላጎት ማዕከል አድርገው እንዲከናወኑ ተደርገዋል፡፡ ለዚህም ነው ለውጡ ከፍ ያለ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎችም የሪፎርም ርምጃዎችን በፍጥነትም፣ በድፍረትም በመውሰድ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ያደረገው፡፡

ለምሳሌ፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው እና በትግል ስልታቸው ምክንያት ከሀገር የተሰደዱ እና ወደ ሀገራቸውም እንዳይገቡ የተደረገ ኃይሎች ሀገራቸው እንዲገቡ መደረጉ አንዱ የሕዝብን ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ የተደረገበት የለውጡ ድፍረት የተሞላበት ርምጃ ነበር፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ አሳሪ እና ፈላጭ ቆራጭ የነበሩ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዘኑ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሻሩ፣ እንዲሻሻሉና አዳዲስ ሕጎችም እንዲወጡ መደረጉ የዚሁ የሕዝብን ጥያቄ መልስ መስጫ ርምጃዎች ናቸው፡፡

የተቋማት ሪፎርም ሥራም፣ ሕዝብን ማገልገል የሚችሉ ነጻ እና ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማትን የመገንባት ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ተግባር ነበር፡፡ በዚህ ረገድ የተሠራው ሥራም በሕዝብ ዘንድ ከፍ ያለ አመኔታን በማትረፍ ሕዝብ የሚተማመንበትን ምርጫ ማካሄድ የቻለ የምርጫ ቦርድን መፍጠር፤ ሀገርን ከመፍረስ የታደገ ኅብረ-ብሔራዊ የመከላከያ ተቋምና ሠራዊትንም መገንባት ማስቻሉ አብነታዊ ማሳያው ነው፡፡

በልማት በኩልም፣ ኢትዮጵያን ከለማኝነት ያላቀቀ፣ ከሸማችነት ያወጣ እና ወደ ሁሉን አቀፍ አምራችነት ያሸጋገረ ተግባር ተሠርቷል፡፡ ኢትዮጵያ ታምርት ተብሎ፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያመርቱ ሆኗል፡፡ በምግብ ራስን እንቻል በሚልም ግብርናው ትርፍ አምራችነትን አጎናጽፏል፡፡ ለምሳሌ፣ ስንዴት ከመሸመት እና ከመለመን ወጥነት፣ ስንዴን ወደ መሸጥና ለርዳታ ወደመላክ ተሸጋግረናል፡፡ በሌማት ትሩፋትና በአረንጓዴ ዐሻራው ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራትም ሕዝብ ምን ያህል የለውጡ ተግባራት እሱን የመሰሉና ያቀፉ መሆናቸውን በተግባር የገለጡ ናቸው፡፡

በመሠረተ ልማት፣ በማኅበራዊ ልማትና ሌሎችም መስኮች የተከናወኑት የዚሁ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው፣ ከለውጡ ማግስት ከ170 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ በጋ ከክረምት የሚያስጉዝ የጠጠር መንገድ፤ እንዲሁም ከ26 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የአስፓልት መንገድ ሥራ መከናወን የተቻለው፡፡ የጤና እና የትምህርት ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች በብዛትም በጥራትም እንዲከወኑ መደረጉም የእነዚህ ልማቶች ትኩረታቸው ሰውን፣ ግባቸውም ሠብዓዊ ልማትን ማምጣት ስለመሆኑ አብነቶች ናቸው፡፡

በዚህ ረገድ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከናወኑ ያሉ፤ ልማትንም ሠብዓዊነትንና ሰውንም ማዕከል ያደረጉ ከገበታ ለሸገር እስከ ገበታ ለትውልድ የዘለቁ፤ አሁን ደግሞ መነሻውን አዲስ አበባ አድርጎ እስከ ገጠር ቀበሌዎች የዘለቀው የኮሪደር ልማት ሥራ፤ መንግሥት እንደ መንግሥት እየሠራቸው ያሉ ተግባራት ሰው ተኮር ስለመሆናቸው ዐቢይ ምስክሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ፕሮጀክቶች (ለምሳሌ፣ የኮሪደር ልማቱ)፤ የአካባቢን መልክና ገጽታ ከመቀየር ባሻገር፤ ዜጎች ምቹ፣ ጤናማና ንጹህ ስፍራ የመኖር መብታቸውን እንዲጎናጸፉ የሚያደርግ ነው፡፡ ምክንያቱም የኮሪደር ልማቱ፣ የተጎሳቆሉ መንደሮች ውስጥ የሚኖሩና ከፍ ላለ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የደህንነት ችግር ውስጥ የኖሩ ወገኖች የተሻለ ኑሮ ወደሚያገኙበት ከባቢ እንዲሸጋገሩ ያደረገ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገርም፣ ዜጎች የሚዝናናኑባቸው፣ በጋራ ቁጭ ብለው የሚመክሩባቸው፣ አብረው የሚራመዱባቸው፣ አረፍ ብለው ሻይ ቡና እያሉ ድካማቸውን የሚወጡባቸው ንጹህና አረንጓዴ ሥፍራዎች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ የሞተር አልባ ተሽከርካሪ መንገዶች በልካቸው የተሰናሰሉበት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማኅበራዊ ፋይዳ አላቸው ተብለው የሚከናወኑ ማንኛውም የልማት ተግባር ከስም የተሻገረ በተግባር የታጀበ፤ ልማት ከሰው የተነጠለ ሕልውና እንደሌለውም እንዲናገሩ ተደርገው እየተከናወኑ ያሉ ሰው ተኮር እንደመሆናቸው፤ እነዚህን ተግባራት በሁሉም ቦታ ላቅ አድርጎ ማስቀጠል የተገባ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የታሪፍ ማሻሻያው ተግባራዊ ቁጥጥር ይጠናከር!!

**ሙዘይን ዘኢትዮጵያ**

የነዳች ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ላይ ጭማሪ መደረጉን ተከትሎ በትራንስፖርት ዋጋ ላይ በቅርቡ ማስተካከያ መደረጉ ይታወቃል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለተሠማሩ ሚኒ ባሶች፣ ሚኒ ባስ ታክሲዎችና የከተማ አውቶብሶች ላይ የአገልግሎት ታሪፍ ማሻሻያ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ የታሪፍ ማሻሻያው ከጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ሲሆን፣ ከዚህ ቀን ጀምሮም አዲሱ የታሪፍ ማሻሻያ ሥራ ላይ እየዋለ ይገኛል ፡፡

የታሪፍ ማሻሻያው ወቅታዊ የነዳጅ ችርቻሮ ዋጋ እና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎችን ያማከለ መሆኑን ቢሮው ገልጿል። የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች አዲስ በተሻሻለው ሕጋዊ ታሪፍ ተመን ብቻ አገልግሎት እንዲሰጡ አሳስቧል። ሕጋዊ ታሪፉን በሚተላለፉ አካላት ላይ ቢሮውና የሚመለከታቸው አካላት ጥብቅ ርምጃ እንደሚወስዱም አስገንዝቦ ነበር፡፡ ህብረተሰቡም ከታሪፍ በላይ የሚያስከፍሉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ሲያጋጥሙ ለትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች፣ ለትራፊክ ፖሊሲና ባቅራቢያ ባለ የትራንስፖርት ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት በአካል ወይም በነፃ የስልክ መስመር 9417 ጥቆማ መስጠት ይችላሉ።

ይህ የተለመደና በየጊዜው በቢሮው በኩል የሚሰጥ መግለጫ ነው። እንዲህ አይነቱን መግለጫና ማሳሰቢያ ከመስጠት በዘለለ ታዲያ ሕጋዊ ታሪፉ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ተግባራዊ ቁጥጥር ማድረግና ከዚህ ውጪ ያፈነገጡ ድርጊቶች ሲፈፀሙ አስተማሪና ሕጋዊ ርምጃ መውሰድን ይጠይቃል። ለተግባራዊው ርምጃ አውን መሆን ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ፣ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችና በተለይ የሕዝብ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው።

እንደሚታወቀው በአዲስ አበባ ከተማ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ ነው። የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶችን ምርጫው ያደረገው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ በአብዛኛው ዝቅተኛ ገቢ ያለው እንደሆነ ይገመታል። ይህ ዝቀተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ለትራንስፖርት ክፍያ ወጪ የሚያደርገው ከእለት ጉርሱና ከቤት ኪራዩ ላይ ቀንሶ ነው። ከሚያገኛት ገቢ ላይ እየሸራረፈ ነው የትራንስፖርት ወጪውን የሚሸፍነው።

ይህ ሆኖ ሳለ ታዲያ ሁሉም ባይሆኑ አንዳንድ ስግብግብ የሚኒ ባስና ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባለንብረቶች ከተቀመጠው ሕጋዊ ታሪፍ በተለይ ጨምረው የሚያስከፍሉ አሉ። ባቋራጭ ነው የምንሄደው፣ መንገዱ አይመችም፣ ነዳጅ ጨምሯል የሚሉና ሌሎች መሠረተ ቢስ ምክንያቶችን እየደረደሩ ከታሪፍ ውጪ ተጨማሪ ሂሳብ የሚያስከፍሉ በርካቶች ናቸው። በዚህ የተነሳ ታሪፉ አይደለም በሚል በረዳቶችና በተሳፋሪዎች መካከል ዱላ ቀረሽ ክርክሮች፣ ውዝግቦችና አለመግባባቶችን በየእለቱ መስማትና ማየትም ተለምዷል።

በዚህ አለመግባባትና ክርክር ደግሞ ተሳፋሪዎች ሰሚ አጥተው ከተጠየቁት ታሪፍ በላይ ከፍለው እየበገኑ ወደ ሥራ ገበታቸው አልያም ወደ ቤታቸው መግባት የዘወትር ሥራቸው ሆኗል። የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ከከተማው ትራንስፖርት ቢሮው ዝርዝር የታሪፍ መረጃ የሚያሳይ ወረቀት በተሽከርካሪው ውስጥ ቢለጥፉም በታሪፉ መሠረት ተሳፋሪዎችን ሂሳብ ሲበሉ አይታዩም፡፡

በዚሁ ወረቀት ላይ ተሳፋሪዎች ከታሪፍ በላይ ሂሳብ ሲጠየቁ በነፃ የስልክ መስመርና በቢሮ ስልክ ደውለው ጥቆማ ለቢሮው እንዲያቀርቡ የሰፈረ ቢሆንም ችግሩ የገጠማቸው ተሳፋሪዎች ሲደውሉ ስልኮች እንደማይነሱም ነው ከብዙ ቅሬታ አቅራቢ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚሰማው። ቢነሱም ቅሬታዎችን ሰምቶ አፋጣኝ ርምጃ ከመውሰድ አንፃር ክፍተቶች ይታያሉ።

ይህ ሲባል ግን በቀረቡ ጥቆማዎች መሠረት ሕጋዊና የእርምት ርምጃዎች እስካሁን ድረስ አልተወሰዱም ማለት አይደለም። ነገር ግን ርምጃዎቹ የአንድ ሰሞን ብቻ ናቸው፡፡ ተከታታይነትም የላቸውም፡፡ በቂም አይደሉም፡፡ ተገልጋዮች በሚያቀርቧቸው ጥቆማዎች መሠረት እነዚህ ርምጃዎች እየተወሰዱ እንኳን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በተለይ ሚኒ ባስ ታክሲዎች ከታሪፍ በላይ ማስከፈላቸውን አሁንም አላቆሙም።

አሁንም ቢሆን ፍራቻው በቢሮው በኩል እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎች በተለሳለሰ ሆኑታ ከቀጠሉ ተገልጋዮች ከታሪፍ በላይ መጠየቃቸው አይቀሬ ነው። አንዳንድ የሕዝብ ትራንስፖር አገልግሎት ሰጪዎችም በዚህ የተለሳለሰ ውሳኔ የልብ ልብ ተሰምቷቸው ይህንኑ ሕገ ወጥ ተግባራቸውን መቀጠላቸውን አያቆሙም። በዚህ መሀል ደግሞ ምስኪኑና በዝቀተኛ ገቢ ራሱን የሚደጉመው የህብረተሰብ ክፍል ገቢው መናጋቱ አይቀርም ።

ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው ሚኒ ባስና ሚዲ ባስ ታክሲዎች ከተቀመጠው ታሪፍ በላይ የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያ ሲጠይቁ ጥቂት ተሳፋሪዎች ብቻ ናቸው ለመብታቸው የሚከራከሩት። እነዚሁ ጥቂት ለመብታቸው የሚከራከሩ ተሳፋሪዎችም በብዙሃኑ ተሳፋሪዎች ግልምጫና ተግሳፅ ሲደርስባቸው ነው የሚታየው። አብረዋቸው ከጎናቸው የሚቆሙና የሚከራከሩትም ጥቂት ናቸው። አብዛኛው ተሳፋሪ ለመብቱ ቆሞ ሲከራከርና ይህን ሕገወጥ ድርጊት በሚፈፅሙ ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ ጥረት ሲያደርግና ሲቃወሙ አይታዩም፡፡ ከዚህ ይልቅ ነገሩን በቸልታ ሲያልፉና ምንም አናመጣም በሚል ተስፋ ሲቆርጡ ነው የሚታዩት።

ስለዚህ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ያልተገባ ታሪፍ ጨምረው ሲያስከፍሉ ለሚመለከተው አካል በመጠቆም ተገቢው ርምጃ እንዲወሰድባቸው ከማድረግ ይልቅ ነገሩን በቸልታ ማለፍ ተገቢ አገልግሎት የማግኘት መብትን አሳልፎ መስጠት ነውና በተሳፋሪዎች በኩል ያለውን ችግር ማረም ያስፈልጋል። ገና ለገና በቢሮው በኩል የሚወሰደው ርምጃ የተለሳለሰና ውጤት የሚያመጣ ስላልሆነ ብቻ አገልግሎት ተጠቃሚው ማህበረሰብ ያልተገባ የታሪፍ ጭማሪ በሚያደርጉ አካላት ላይ የሚያደርገውን ጥቆማ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ያልተገባ የታሪፍ ጭማሪ በሚያደርጉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ሕጋዊና አስተማሪ ቅጣት እንዲወሰድ በማድረግ ረገድ ትልቁንና ዋናውን ድርሻ ሊወጣ የሚገባው የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ነው። ቢሮው እስካሁን ድረስ ከታሪፍ በላይ በሚያስከፍሉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ሲወስዳቸው የነበሩ ርምጃዎች እንዳሉ ሆነው አሁንም ቢሆን ይህን ርምጃውን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ።

በተለይ ደግሞ እንዲህ አይነት ያልተገቡ የታሪፍ ጭማሪዎች በትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ ተደርገው ወደቢሮው ጥቆማ ሲደርሱ ለጥቆማዎቹ ፈጣን ምላሽ በመስጠት የሚታይ፣ አስተማሪና ሕጋዊ የእርምት ርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል። ምክንያቱም በድርጊት የሚገለፁና የሚታዩ ርምጃዎች በተወሰዱ ቁጥር ያልተገባ የዋጋ ታሪፍ ጨምረው የሚያስከፍሉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን ወደሕጋዊ መስመር ስለሚመልስ ነው።

ምንም እንኳን በዚህ ጊዜ በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ያልተገቡ የታሪፍ ጭማሪ ክፍያዎች መልካቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየተለዋወጠና እየረቀቀ ቢመጣም በቢሮው በኩል የሚወሰዱ ርምጃዎች ይህን መሠረት ያደረጉ፣ ጊዜውን የዋጁና በጥናት የተደገፉ ሊሆኑ ይገባል። ይህ ሲሆን ጤናማና ፍትሃዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ይኖራል፡፡

ከዚህ ባሻገር በዚህ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሂደት የትራፊክ ፖሊሶች ያልተገባ የታሪፍ ዋጋ በተገልጋዮች ላይ እንዳይጨመር በመቆጣጠርና በመከላከል ረገድ ትልቅ ድርሻ አለባቸው። በተለይ የትራፊክ ፖሊሶች ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች ቅርብ እንደመሆናቸው ያልተገባ የታሪፍ ጭማሪ ተገልጋዮች ሲያጋጥማቸው ለቢሮው ከሚያደርጉት ጥቆማ በተጨማሪ ለትራፊክ ፖሊሶችም የሚጠቁሙበት እድል ስለሚኖረው ወደነርሱ ሲመጡ ቀና ትብብርና ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል። ከቻሉ ችግሩ እዛው እንዲፈታ ካልሆነ ደግሞ ለሚመለከተው ቁጥጥር አካል በመደወልና መረጃ በመስጠት ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ መተባበር ይኖርባቸዋል።

እነዚህ ሶስት አካላት ማለትም የከተማው ትራንስፖርት ቢሮ፣ አገልግሎት ተጠቃሚው ህብረተሰብና ትራፊክ ፖሊሶች በጋራና በቅንጅት ቢሠሩ ብሎም ያልተባ የታሪፍ ዋጋ ጭማሪ ሲታይ ሕጋዊና አስተማሪ ርምጃ ቢወሰድ በዚህ ረገድ የሚታየውን ችግር ማስቆም ይቻላል። ማቆም ባይቻል እንኳን መቀነስ ይቻላል ። ከዚሁ ጎን ለጎን ታዲያ በተቀመጠው ሕጋዊ የትራንስፖርት ታሪፍ መሠረት ተገልጋዩን ህብረተሰብ በቅንነትና በትጋት የሚያገለግሉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልሎት ሰጪዎችን ማድነቅ ተገቢ ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትለው የሚያገለግሉ ናቸውና!!

ዜና

# በኢንዱስትሪ ፓርኩ...

ከ2ኛው ገጽ የዞረ

ያመረተው የአቮካዶ ዘይት ወደ ጣልያን ሀገር መላኩን ገልፀው፤ ቴክኖሎጂ በማሸጋገርና በሥራ ዕድል ፈጠራ ካለው አስተዋፅኦ ባለፈ የአቮካዶ ዘይት ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ መጀመሩ በእድገትና ሽግግር ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ አመላካች መሆኑን ጠቁመዋል።

ፓርኩ ወደ አስር የሚጠጉ ምርቶች ቡና፣ ወተት፣ እንቁላል እና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ መሰማራር ለሚፈልጉ አልሚ ባለሀብቶች ክፍት መሆኑን ገልፀው፤ አሁን ላይ ፍላጎት ካሳዩ ባለሀብቶች ጋር የሥራ ስምምነት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል። በመሆኑም በቡናው ዘርፍ ለመሠማራት ጥያቄ ያቀረበ ባለሀብት በፓርኩ ውስጥ ቦታ ተሰጥቶት ወደ ሥራ መግባቱን አመልክተዋል።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮፖሬሽን ሁለቱም ፓርኮች በጌዲዮ ዞን ዲላ ከተማ እና ይርጋጨፌ ላይ እያለማ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ የይርጋጨፌ ቡና ታዋቂ በመሆኑ የማምረት አቅም በማሻሻል ምርትን ከፍ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በቀጣይ አቅሙን በማጠናከር በሶስት ሽፍት እየሠራ በዓመት ከ130 ቶን በላይ የአቮካዶ ዘይት ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተቀናጀ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አስረድተዋል።

ፓርኩ በውስጥ ከፈጠረው የሥራ እድል ባለፈ በግብዓት አቅርቦት ትስስር ከሶስት ሺህ በላይ የአካባቢውን አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ማድረጉን ጠቅሰው፤ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስተሮች የክልሉን ፀጋ ተጠቅመው እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል።

## እርማት

ትናንት በወጣው የግብርና ሚኒስቴር 100 ቀናት አፈፃፀም ዜና ላይ ‹‹በግብርና የሶስት ወራት የወጪ ንግድ የተገኘው አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ሳይሆን 976 ሚሊዮን ዶላር›› ተብሎ እንዲነበብ ከትህትና ጋር እንገልፃለን ለተፈጠረው ስህተትም ይቅርታ እንጠይቃለን።

# በብሪክስ ማሕቀፍ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሰሞኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ አዘጋጅነት ‹‹በብሪክስ ማሕቀፍ ውስጥ የኢትዮጵያ ሚና›› በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ተካሂዷል። በውይይቱ እንደተገለጸው፤ ብሪክስ የፖለቲካና የጸጥታ፣ የኢኮኖሚና የፋይናንስና የሕዝብ ለሕዝብና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላሉ ሀገር ብዙ ጠቀሜታ አለው። የትብብሩ መገለጫዎች ከሆኑት መካከል አዲስ የልማት ባንክ ተቋቁሟል።

ባንኩ ለታዳጊ ሀገራት ለመሠረተ ልማትና ለዘላቂ ልማት የገንዝብ ድጋፍና የፋይናንስ አቅርቦት የሚያደርግ ነው። ከተመሠረተበት እ.ኤ.አ. ከ2015 ጀምሮ እስከ 2021 25 ቢሊዮን ዶላር ለሀገራቱ አቅርቧል። ባለፈው ዓመት ብቻ አምስት ቢሊዮን ዶላር አካባቢ ያቀረበ ሲሆን የስብሰቡ ውጤታማነት አንድ ማሳያ ነው። በቀጣይ ኢትዮጵያ ለጀመረችው የእድገት ጉዞ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌድዮን ጢሞትዮስ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው ብሔራዊ ጥቅሟን ይበልጥ ለማሳደግ ነው። የብሪክስ ስብስብ እየተጠናከረ ሲሄድ ብዙ ሀገራት ብሪክስን የመቀላቀል ፍላጎት አሳይተዋል። ተደጋጋሚ ጥያቄዎች እያቀረቡም መጥተዋል። በነባር የስብስቡ ሀገራት መካከል የትኞችን ሀገራት ማካተት አለብን? እና አዲስ አባል ሀገራትን በምን መንገድ መቀበል እንደሚገባ ሰፊ ውይይት አድርገዋል። በመጨረሻም የስብስቡን ዓላማ ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ተፅዕኖ ፈጣሪ ናቸው ያሏቸውን ሀገራት ብቻ ተቀብለዋል። ከዚህ ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት፤ ይህም የሚያሳየው በዓለም ደረጃ የኢትዮጵያ ተፈላጊነት ከፍተኛ መሆኑን ነው።

ኢትዮጵያ ብሪክሰን የተቀላቀለችበት ሦስት ምክንቶች አሏት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ በፍጥነት በማደግ ላይ ኢኮኖሚ ባለቤት ናት። እድገትን ለማሳለጥ የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ ድጋፍና ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል። ከላይ የተጠቀሱትን ለማግኘት የብሪክስን ስብስብ መቀላቀልና ስብስቡ ይዞት የሚመጣውን እድል ለመጠቀም መፈለግ ከምክንያቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ያመለክታሉ።

ሁለተኛው ምክንያት ወሳኝ በሆኑ ዓለም አቀፍ አጀንዳዎች ላይ የሚመካከርና የጋራ አቋም የሚይዝ ስብስብ ሲሆን በተለይ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ ምን መምሰል አለበት በሚለው፣ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ይበልጥ አካታች፣ ፍትሐዊ እንዲሆኑ፣ የታዳጊ ሀገራትን ፍላጎት የሚያሟሉና ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ እንዴት መሻሻል በሚኖርባቸው ጉዳዮች ላይ አቋም የሚያዝበት ስብስብ በመሆኑ ነው። ኢትዮጵያ የዚህ ስብስብ አባል በመሆን ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበርና የአፍሪካን ፍላጎትና ድምጽ ለማሰማት የምትችልበት ጠቃሚ እድል ይፈጥራል ብለዋል።፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመን ያስቆጠረ የዲፕሎማሲ ታሪክ ያላት ሀገር ናት። በርካታ የዓለም ሀገራት ችግር ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የሊጎፍኔሽን አባል ነበረች። ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ነጻ ባልነበሩበት ጊዜ በርካታ የዲፕሎማሲ ታሪክ ያላት በመሆኑ በብሪክስ ስብስብ ውስጥም ለአፍሪካ ሀገራት ድምጽ ለመሆን ወደ ስብስቡ ገብታለች። እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥራች አባል ሀገር ናት። ይህን ታሪክና ባህል በማስቀጠል ዓለም አቀፍ ሥርዓቱ ማስተካከልና የአፍሪካን ድምጽ በመሆን ለመሳተፍ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የብሪክስ ስብስብ ውስጥ ኢትዮጵያ አባል ባትሆን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም በተቃራኒ መንቀሳቀስ ለሚፈልጉ አካላት ሜዳው ይለቀቃል። ኢትዮጵያ በሌለችበት በኢትዮጵያ ላይ የፈለጉትን አቋም ሊያራምዱ ይችላሉ። ይህን አይነት አሉታዊ እንቅስቃሴ ለመከላከል በብሪክስ ማሕቀፍ ውስጥ መገኘት ለብሔራዊ ጥቅም በጣም ወሳኝ ነው። አባል ለመሆን የተደረገው ጥረትም ተሳክቶ ውጤት እያመጣ መሆኑንም ሚኒስትሩ ይጠቅሳሉ።

የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ለመሆን ከደቡብ አፍሪካው ስብስባ ቀደም ብሎ በርካታ የዲፕሎማሲ ሥራ ሠርታለች። ኢትዮጵያ የሌለችበት ስብስብ አፍሪካን ሰብስቤያለው ብሎ መውሰድ እንደማይቻል የማስረዳት ሥራ በሚገባ የተሠራ ሲሆን ውጤት አምጥቷል።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በአፍሪካ ህብረት ምሥረታ፣ ለአፍሪካና ለዓለም ሰላም የነበራት ሚና፣ የሕዝብ ቁጥር ብዛት፣ እያስመዘገበች ያለው የኢኮኖሚ እድገት፣ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ መሆኗ ግምት ውስጥ በመግባት አባል እንድትሆን የተደረገው ጥረት ለውጤታማነቱ ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ይናገራሉ።

እንደ አምባሳደር ሬድዋን አባባል፤ የብሪክስ አባልነት ብዙ ጥረትን የጠየቀና ሊቀር የሚችልበት እድልም ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ደቡብ ለብሪክስ አባል ሀገራት መሪዎች ኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ደረጃ ያላትን ተጽዕኖ በመግለጽ ያደረጉት ጥረት ጉልህ ነው። አሁን ላይ አዲስ ለአባልነት የሚጠይቁ ሀገራትን የማስገባትና ያለማስገባት ሁሉም ድምጽ በድምጽ የመሻር መብት አለው። ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት የስብስቡ አባል ባትሆን ከነጭራሹ የማትገባበት እድል ነበር። ብሪክስ ከኢኮኖሚ ደረጃ አንጻር፣ በፖለቲካ አማራጭነት፣ በደቡብ ለደቡብ ትስስር፣ የገንዝብ ርዳታ ከማግኘት አንጻር ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ነው። አባል መሆን በዓለም መድረክ ተጽእኖን ይጨምራል፣ ወዳጅ የማብዛት አቅም፣ ኢንቨስትመንትንና የገንዝብ ድጋፍን ያሳድጋል።

ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የከተማ ነዋሪዎች ተሳትፎ

አብርሃም ሳሙኤል

በአሁኑ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው የከተማ ግብርና የልማት ሥራ የቤተሰብ ብልጽግናን ከማረጋገጥ አኳያ የማይተካ ሚናን እየተጫወተ ነው። ይህ ተግባር ኢኮኖሚውንም እያሰፋ በሀገር ደረጃ በራስ አቅም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እያስቻለ ይገኛል። ከዚህ አንጻርም ነው የከተማ ግብርና የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥና የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው የሚባለው። ከዚህ ሻገር ስንልም ይህ ተግባር ገቢ ማስገኛ መንገድም ሆኖ ብዙዎችን ተጠቃሚ እያደረገ ነው። በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች በአነስተኛ የከተማ ግብርና ልማት ሥራዎች ላይ በመሠማራት የምግብ ፍላጎታቸውን ከመሸፈን አልፈው የገቢ ምንጭ መሠረታቸውን እየጣሉ ይገኛሉ። የከተማ ነዋሪዎች ተሳትፎን ከፍ በማድረግም ለሥራ ዕድል ፈጠራ ትልቅ አቅም እየሆነም ነው።

ይህንን ከሚያሳዩ ከተሞች መካከል ደግሞ የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር አንዱ ሲሆን፤ በግብርና መምሪያው በኩል የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥ በተለይም በከተማ ግብርና ልማት ሥራ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ እንደሆነ የሃዋሳ ከተማ ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አበባየሁ ላሊማ ይገልጻሉ። እርሳቸው እንዳሉት፤ በ2017 ዓ.ም በከተማ ደረጃ የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ሰፋፊ ተግባራት ተከናውነዋል። አንዱ የቤተሰብ ብልጽግን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ቤተሰብ በዚህ ተግባር ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ነው። ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ቤተሰብ የራሱ ድርሻ እንዲኖረው ሥራዎች ተከናውነዋል።

አቶ አበባየሁ፣ በዶሮ፣ በንብ ማነብ፣ በእርሻ ሥራ፤ በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የሀር ምርትን ጨምሮ የቤተሰብ ሕይወትን የሚያሻሽሉ የልማት ሥራዎች እንደ ከተማ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራበት ስለመሆኑም ያብራራሉ። በከተማው ውስጥ በበጀት ዓመቱ በዶሮ ምርት የአንድ ቀንና የ48 ቀናት የዶሮ ጫቹቶችን በማሳደግ ለአርሶ አደሮች እየተከፋፈለ ስለመገኘቱም ይጠቅሳሉ።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፣ በከተማ ውስጥ በ32 ቀበሌዎች 40 የዶሮ መንደር በመፍጠር በማህበር የማደራጀት ተግባር ተከናውኗል። በበጀት ዓመቱ 2 ሚሊዮን የዶሮ ጫጩት ለማሠራጨት ዕቅድ ተይዞ፣ በሩብ ዓመት 357 ሺህ 92 ጫጩቶችን ለማህበረሰቡ ለማከፋፈል ተችሏል። አፈጻጸሙንም 82 ነጥብ 2 በመቶ ነው። እንዲሁም 1 ሚሊዮን 72 ሺህ 903 እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን ለማከፋፈል ታቅዶ፣ እስካሁን ባለው አፈጻጸም 396 ሺህ 535 የሚሆኑትን ዶሮዎችን ተሠራጭቷል። በዚህ ረገድ በዶሮ ምርት በዓመቱ ከ14 ሚሊዮን በላይ እንቁላል ለማሰባሰብ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛልም።

ሌላው በከተማ ግብርና ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ አንዱ የእንስሳት ዝርያ የማሻሻል ሥራ ሲሆን፣ 16ሺ 23 ከብቶች ዝርያ ለማሻሻል ዕቅድ ተይዞ፣ ባለፉት ሰስት ወራት ውስጥ በሰው ሠራሽ ዘዴ 8 ሺህ 581 ከብቶች ዝርያ ተሻሽሏል። በተጨማሪም 1 ሺህ 455 ከብቶችን ዝርያቸው በተሻሻሉ በሬዎች የማዳቀል ሥራም መከናወኑን ኃላፊው አክለዋል። በከተማና በከተማ ውስጥ በታቀፉ ገጠር ቀበሌዎች ውስጥ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግም የንብ ማነብ ተግባር እየተከናወነ ሲሆን፤ በአምስት ቀበሌዎች የንብ ቀፎ በማሰራጨት የማር ምርት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።



አቶ አበባየሁ ላሊማ የሃዋሳ ከተማ ግብርና መምሪያ ሃላፊ

በመቀጠልም የሀር ምርት እንዲስፋፋ ለማድረግ በተመረጡ በሁለት ቀበሌዎች አርሶ አደሮችን በማለማመድ ምርት እንዲያመርቱ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አቶ አበባየሁ አስረድተዋል። ምርቱ እንዲስፋፋ የሀር ትል እየተሰራጨም እንደሚገኝ ጠቅሰዋል። የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥ በዓመቱ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ሌላኛው ሥራ የእርሻ ሥራ ሲሆን፤ እርሻው በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ 558 ሄክታር መሬት ላይ በተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬ ዘሮች እየለማ እንደሆነ በመጠቆም፣ በዚህም 558 ሺህ ኩንታል ምርት ለማግኘት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ተናግረዋል።

በከተማ ውስጥ ባለው ቦታ 346 ሺህ ዕቃ ላይ በተለምዶ (ቨርቲካል ፋርም) የሚባለውን ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ቶሎ የሚደርሱትን እንደ ቆስጣና ሌሎች የጓሮ አትክልቶችን መዝራት መጀመሩን ያነሱት ኃላፊው፤ ይህ ሥራ የሚስተዋለውን የምርት አቅርቦት ችግር በብዙ መልኩ ፈቶታል። እንዲሁም የበጋ መስኖ ሥራም በከተማ ውስጥ ተግባረዊ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ስለሆነ ውጤቱ በብዙ መልኩ እየታየ መጥቷል ብለዋልም።

በተለያዩ የከተማ ግብርና ዘርፎች እንደ ከተማ ሥራዎች መሠራታቸው በርካት ያሉ ውጤታማ ተግባራትን እንዳሳየ የገለጹት አቶ አበባየሁ፣ የመጀመሪያው ሰዎች ከዘርፉ ተጠቃሚ እየሆኑ መምጣታቸው ነው ይላሉ። 39 ሺህ 635 የከተማ ነዋሪዎች ተሳታፊ ተጠቃሚም እንደሆኑም ያነሳሉ። በየደረጃው ላሉ ለ1 ሺ575 የሚሆኑ ዜጎችም የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥም ምቹ ሁኔታዎች እንዲኖሩ አስችሏል። የተያዘው ዕቅድ ግብ እንዲመታም መደላደል መፍጠሩን አስረድተዋል። ይሁን እንጂ ተግባራቱ በውጤታማነታቸው እንዲቀጥሉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መረባረብ እንዳለበት አሳስበዋል።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ብሪክስን እንደ እድል

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሩሲያ ካዛን ከተማ እየተካሄደ ባለው 16ኛው የብሪክስ ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ስብሰባው የባለብዙ ወገን የዓለም ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ሀገራት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች መፍታት የሚችሉበት ተስፋ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አዲስ የብሪክስ አባል እንደመሆኗ በፍትሃዊነት መርህ ያደጉ እና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ያማከለ ባለብዙ ወገን ትብብር እንዲጎለብት ለማድረግ ትሰራለች፡፡ ዓለማችን የባለብዙ ወገን ትብብሮችን በሚፈልጉ በርካታ ቀውሶች ውስጥ እያለፈች መሆኗን አውስተዋል።

አበው "ነገርን ነገር ያነሳዋል" እንዲሉ የብሪክስን ታሪካዊ ዳራ ከገለልተኛ ሀገራት ንቅናቄ ጀምሮ ወደ አነሳሁበት መጣጥፌ ልመልሳችሁ። በጎርጎሮሳዊያኑ የዘመን አቆጣጠር በ1950ዎቹ የአሜሪካንና የሶቭየት ሕብረትን መሳሳብ ለመቃወም 120 ሀገራት የገለልተኛ ሀገራትን ንቅናቄ ፈጥረዋል። ደርግ ጭልጥ ብሎ የሶቭየቱን ጎራ ተቀላቅሎ የነበር ቢሆንም ዛሬም ሀገራችን የዚህ ንቅናቄ አባል ናት። ይህ ስብስብ ከዓለም ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የያዘ። ከጥቅል የዓለም ምርት ደግሞ የአውሮፓ ሕብረትን በልጦ 18 በመቶ ድርሻ ያለው ነው። ይሁንና የተፈለገውን ያህል ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። ለዚህ ነው ብሪክስ ወደፊት የመጣው።

የብሪክ/BRIC ስረወ-ምህጻረ ቃልም ሆነ ጽንሰ ሃሳብ የተፈጠረው በጎልድማን ሳክስ የኢኮኖሚ ባለሙያ ጂም ኦኔል በጎርጎሮሳዊያኑ አቆጣጠር 2001 ዓ.ም ሲሆን፤ ብራዚልን፣ ራሽያን፣ ሕንድና ቻይናን ያካተተ የኢኮኖሚ ስብስብ ሃሳብ ነው። ይህ እሳቤ በ2009 ዓ.ም እውን ሆነ። በዓመቱ 2010 ዓ.ም ደቡብ አፍሪካን አካቶ ብሪክስ/BRICS ሆነ። የምዕራባውያን ጉልሃን ወይም ኤሊቶች በስብስቡ የቻይናን የበላይነት ለመግለጽ ብሪክስን ቻይና ሲደመር አራት ወይም China + 4 ይሉታል።

በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ በተካሄደው የብሪክስ 15ኛ ጉባኤ ሀገራችንን ጨምሮ ስድስት አዲስ አባላትን ሲጨምር ደግሞ "China + 10" የሚል ተለዋጭ ስያሜ ሰጥተውታል። ብሪክሶች ግን "BRICS PLUS" ማለትን መርጠዋል። ምዕራባውያን እነሱ ቡራኬ ያልሰጡትን ስብስብ እንዲህ በነገር ይሸነቁጡታል።

በ"The Ethiopian Economist View" ድረ ገጻቸው ቢዝነስ፣ ኢኮኖሚክስና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመጻፍ፤ ማህበራዊ ሚዲያውን በተለይ ፌስቡክን ለበጎ ዓላማ በማዋል የሚታወቁት የኢኮኖሚክስ ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ፤ የተጨመሩት 6 አዲስ አባል ሀገራት በጠቅላላ 410 ሚሊየን ሕዝብ ያላቸው በመሆኑ የአባል ሀገራት ሕዝብ ብዛትን ወደ 4.2 ቢሊየን ያደርሱታል።

ነባር አባል ሀገራቱ ያላቸው ጠቅላላ የምርት መጠን GDP 26 ትሪሊዮን ዶላር ይደርሳል። ከዓለም ጠቅላላ ምርት መጠን ውስጥ 35 ከመቶ ነው። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ እስከ ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ድረስ የነበረው የዓለም ሀገራት በርዕዮተ ዓለም የመቧደን አይነት አዝማሚያ ያለው የሚመስል ሆኖ አባል ሀገራቱ በዚህ ወቅት ዓለም በጥቂት ሀገራት የበላይነት መመራቷ ማብቃት አለበት ሲሉ ይሞግታሉ።

አዲሱን አሰላለፍ ወይም BRICSን የመቀላቀል ዕድሎችንና ስጋቶችን ማመዛዘን ይገባል፡፡ እድሎች፡- የተሻሻለ የኢኮኖሚ ትብብር ሊፈጠር ይችላል። ለኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ንግድን፣ የውጪ ኢንቨስትመንትን እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማጎልበት ኢኮኖሚያዊ ትብብር እንዲጨምር ያደርግ ይሆናል። ይህ አጋርነት ቀጣይነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማትን ማበረታታት፣ የሥራ እድል መፍጠር እና ፈጠራን ማጎልበት በመጨረሻም የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። የመሠረተ ልማት ግንባታ ተስፋዎች ሊኖሩት ይችላል። ለዚህ ነው ብሪክስን እንደ መልካም አጋጣሚ እንደ እድል መጠቀም ያሻል የሚባለው።

የBRICS አባል ሀገራት በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ከፍተኛ እውቀት እና ሀብቶች አሏቸው። ኢትዮጵያ ህብረቱን በመቀላቀሏ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ጉድለትን ለመፍታት ወሳኝ የሆነውን ሀብት፣ እውቀት እና ልምድ ልታገኝ ትችላለች። ከአዲሱ የBRICS ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማፋጠን አስደሳች ዕድል ሊፈጥርላት ይችላል ይሉናል ባለሙያው። ይህን እድል ወደ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለመቀየር ጠንካራ የማምረት አቅም መፍጠር ያስፈልጋል።

ብሪክስ በተነሳ ቁጥር በስጋትነት የሚወሳው፤ የብሪክስ አባልነትን ተከትሎ የምዕራብ ሀገራትም ሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት በውሳኔው ደስተኛ ላይሆኑ ይችላሉ። በዚህ የተነሳም ብድር እና ርዳታ ሊከለክሉ ይችላሉ። ሆኖም ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋሙም ሆነ ዓለም ባንክ ብሪክስን በቅርብ ለተቀላቀለችሁ ሀገራችን ብድር ከመስጠት ወደ ኋላ አላሉም። ሆኖም ስጋቱ ምክንያታዊ ነው።

BRICSን መቀላቀል የንግድ መዳረሻዎችን ወደ አባል ሀገራት ገበያዎች አቅጣጫ እንዲቀይር ሊያደርግ ይችላል። ይህ ለረጅም ጊዜ የቆየውን የኢትዮጵያ እና የምዕራባውያን እና የአሜሪካ የንግድ ግንኙነቶችን ሊያደናቅፍ ይችላል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ የውጭ ገበያ መዳረሻዎቿን በማስፋት የንግድ ልውውጥ እንዲጨምር እና በነጠላ የንግድ አጋሮች ላይ ያላትን ነባር ጥገኝነት እንዲቀንስ አዳዲስ ዕድሎችን ሊከፍትላትም ይችላል።

ይሁን እንጂ በBRICS ውስጥ የተመሰረተው አዲስ የልማት ባንክ አማራጭ የፋይናንስ ዘዴዎች መፈጠራቸው እነዚህን ሥጋቶች ለመፍታት እና ለኢትዮጵያ ለመሠረተ ልማትና ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ካፒታል ወይም የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ ሊያግዛትም ይችላል። ከዚህ ቀደም ዩናይትድ ስቴትስ እና አንዳንድ ምዕራባውያን ኃያላን የአፍሪካ ሀገራት ከBRICS ጋር መስማማታቸው ስጋታቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የBRICS ታዋቂነት እያደገ በመምጣቱ ዩናይትድ ስቴትስ በአፍሪካ ላይ ያላት ተጽእኖ እየቀነሰ እንዳይሄድ ትሰጋለች። ስለሆነም አጋርነትን ማጠናከር፣ የርዳታ ፖሊሲዎቻቸውን ማሻሻል ወይም ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ጫና ፈጣሪ ርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ ይሉናል አቶ ዋሲሁን።

የአሜሪካው ኢንቨስትመንት ባንክ ጎልድማን ሳክስ በሚቀጥሉት 50 ዓመታት የብሪክስ አባል ከሆኑ ሀገራት ቻይናና ሕንድ አሜሪካንን ቀድመው እንደ ቅደም ተከተላቸው በኢኮኖሚያቸው ዓለምን ይመራሉ ሲል ይተነብያል። ኢትዮጵያም በ6 ነጥብ 2 ትሪሊየን ዶላር ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት 17ኛ ደረጃ ላይ እንደምትቀመጥ ባንኩ አክሎ ጠቁሟል። ይህን ተስፋ የሰነቀች ሀገር አበክራ ብሪክስን ለመቀላቀል ማመልከቷና ተቀባይነትን ማግኘቷ ተገቢ ውሳኔ ብቻ ሳይሆን አርቆ አስተዋይነት ወይም ስትራቴጂካል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

የዓለም የንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ደጅ ስትጠና ሶስት አስርት ዓመታትን ላሳለፈች ሀገር፤ አሜሪካ ኢፍትሐዊ በሆነ አግባብ ከአጎዋ ወይም AGOA/The African Growth and Opportunity Act/ማለትም ከሰሃራ በታች ለሚገኙ ሀገራት ምርቶቻቸውን ከቀረጥ ነፃ ለአሜሪካ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሚያስችል ዕድል ለታገደች ሀገር ፤ ብሪክስን መቀላቀሏ ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው። ለመሆኑ ይሄ ለብልጽግና ለእድገት ስትራቴጂካዊ መነሻም መውጫም የሆነው ብሪክስ ማን ነው።

**ጂኦፖለቲካው ውጥረት፣ የንግድ ግጭቶችና የሚከተሉት የኢኮኖሚ ሥርዓት ለስብስቡ አንድነት ስጋቶች ናቸው። ያም አለ ይህ ብሪክስ በማደግ ላይ ላሉት 11 ሀገራት ድምጽም መድረክም ነው**

"ብሪክስ" ወይም "BRICS" የሚለው ምህጻረ ቃል በማደግ ላይ ያሉ የአምስት ሀገራትን ስብስብ የሚወክል ሲሆን የየሀገራቱን የመጀመሪያ ሆሄ በመውሰድ የተፈጠረ መጠሪያ ነው። 'B'ን ከBrazil ፣ 'R'ን ከRussia ፣ 'I'ን ከIndia ፣ 'C'ን ከChaina በመጨረሻም 'S'ን ከSouth Africa በመውሰድ "BRICS"የሚለው ስያሜ ተመሠረተ። መጠሪያው የተፈጠረው በ2001 ዓ.ም ጂም ኦኔል በተባለ የኢኮኖሚክስ ጠበብት ሲሆን እነዚህ ሀገራት በ21ኛው መክዘ በዓለም ኢኮኖሚ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሚሆኑ ተንብየው ነበር። ከ22 ዓመታት በኋላ ዛሬ ያረጋገጥነው ትንበያው ጠብ ያላለና ትክክለኛ ሆኖ መሆኑን ነው።

የብሪክስ ሀገራት በተለያየ የጂኦግራፊ ክልል የሚገኙ ሲሆኑ፣ የሕዝብ ብዛታቸው ከ3 ቢሊየን በላይ ወይም ከዓለማችን ሕዝብ 45 በመቶውን የያዙ ፤ ከዓለማችን መሬት ወይም የብስ 26 በመቶ የሚሸፍኑ፤ ከዓለማችን ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት 35 በመቶ ድርሻ ያላቸው ናቸው። የተመሠረተበት ዋና ዓላማ በሀገራቱ መካከል ትብብር ለመፍጠርና ለመመካከር ነው። እርስ በርስ ለመነገድ፣ ኢንቨስት ለማድረግና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማሳለጥ የተቋቋመ ስብስብ ነው። በየጊዜው በመደበኛነት በመሰባሰብ ስለ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ቀጣይነት ስላለው ልማት፣ ስለዓለም አቀፍ አመራርና ጸጥታ ይመክራሉ። ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ።

ብሪክስ ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ ብሪክስ ባንክ የተሰኘ አዲስ ባንክ ማቋቋም ነው። ባንኩ ለአባል ሀገራቱ ሆነ ለሌሎች ለመሠረተ ልማት ግንባታ እና ቀጣይነት ላላቸው ልማቶች ብድር ያቀርባል። በአሜሪካና በምዕራባውያን ቅድመ ሁኔታዎችና እጅ ጥምዘዛዎች ስር ከወደቁት የዓለም ባንክና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ተጽዕኖ በመላቀቅና አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ኢነርጂ፣ ጤናና ትምህርት ላይ በስፋት የመሥራት ዕቅድ አለው። በሀገራቱ መካከል ትብብርንና የልምድ ልውውጥን ለማሳለጥ የጋራ ፎረም መመስረቱን ሰነዶች ያወሳሉ።

በአባላቱ መካከል መተባበርና መደጋገፍ እንዳለው ሁሉ ተግዳሮቶችና ልዩነቶችም አሉ። እያንዳንዱ ሀገር የየራሱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ባህሪ ያለው መሆኑ የመጀመሪያው ተግዳሮት ሲሆን የጋራ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት ወይም የየሀገራቱ ፍላጎት በእኔ እብስ በእኔ እብስ የሚሳሳቡበትና የሚራኮቱበት መድረክ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋትም አለ።

ጂኦፖለቲካው ውጥረት፣ የንግድ ግጭቶችና የሚከተሉት የኢኮኖሚ ሥርዓት ለስብስቡ አንድነት ስጋቶች ናቸው። ያም አለ ይህ ብሪክስ በማደግ ላይ ላሉት 11 ሀገራት ድምጽም መድረክም ነው። ስጋታቸውን የሚያሳስቡበት፣ ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበት፣ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተገቢውን ስፍራና ትኩረት እንዲያገኙ የሚጠይቁበት የጋራ መድረክ ነው።

የብሪክስ አባል ሀገራትን ከፖለቲካ ይልቅ ምጣኔ ሀብት እንዳስተሳሰራቸው ተደጋግሞ ታይቷል። ከሰሞኑ የአባል ሀገራቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በደቡብ አፍሪካ ተገናኝተው ነበር። በዚህ ወቅትም ዓለም በምዕራባዊያን ከሚዘወረው ሥርዓት መውጣት እንዳለባት አንስተዋል። የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ናሌዲ ፓንዶር፤ ቡድኑ በጂኦፖለቲካ ውጥረት፣ በእኩልነት አለመኖር እና በደኅንነት ስጋት ውስጥ ላለው ዓለም ሃሳብ ይዞ መቅረቡን ገልጸዋል።

የሕንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በበኩላቸው ሱብራህማንያም ጃይሻንካር ስብስቡ ዓለም ባለብዙ መልክ ስለሆነች ባረጀው መንገድ አዲሱን አጀንዳ መፈጸም አይቻልም። ከምንጋፈጣቸው ችግሮች አንዱ የምጣኔ ሀብት ጉዳይ ሲሆን ብዙ ሀገራት በጥቂቶች በጎ ፈቃድ እንዲኖሩም ሆነዋል ብለዋል።

ብሪክስ ሲቋቋም ጂኦኢኮኖሚያው አሰላለፍ ተደርጎ ቢወሰድም ራሽያና ቻይና በአንድ ወገን አሜሪካና ምዕራባውያን በሌላ ወገን የገቡበት ፍጥጫና ግብግብ ብሪክስ ወደ ጂኦፖለቲካዊ ኃይል እንዳያጋድል እያሰጋ ይገኛል። የኢራን ወደ ቡድኑ መቀላቀል ደግሞ ለእስራኤልና ለአሜሪካ ምቾት የሚሰጥ ጉዳይ ካለመሆኑ ባሻገር፤ ዩኤኢና ሳውዲ አረቢያ ከአሜሪካ ጉያ ወጥተው ወደ ቻይና ማዘንበል መጀመራቸው በተለይ አሜሪካ ላይ ስጋት መፍጠሩ አይቀርም።

ራሽያና ቻይና በአደባባይ ብሪክስ G- 7 ለመገዳደር የተቋቋመ ነው ማለታቸው የተቋቋመለት ዓላማ እንዳያስተው ስጋት መፍጠሩ አልቀረም። ይህን በመፍራት ይመስላል ሕንድና ብራዚል ተሽቀዳድመው ብሪክስ G-7 ለመገዳደር ሳይሆን በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት አለኝታ እንዲሆን ነው ሲሉ ያስተባበሉት። ዳሩ ግን አባል ሀገራቱ የቻይናም ሆነ የራሽያ መሳሪያ ተደርገው እንዳይታዩ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

ሻሎም ! አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ለወገን የተከፈለ መስዋዕትነት

ሰሚራ በርሀ

በጥሩ ትስስር እና መረዳዳት ባለበት የማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ነው ያደገችው። በዚህም ስለሌሎች ይመለከተኛል የሚለውን ሃሳብ በውስጧ ይዛ ኖራለች። ከሰባት ዓመት በላይ በጋዜጠኝነት ሙያ አገልግላለች። ለዓመታት ኑሮዋን ከኢትዮጵያ ውጭ አድርጋ ቆይታለች። ከቆየችበት የውጭ ሀገር ስትመለስ ኢትዮጵያ ያላትን ባሕል እና ወግ ሥነ-ምግባር ያለውን ዋጋ ለብዙዎች ለማሳየት የራሷን ፕሮግራም ጀመረች። ይህ የጋዜጠኝነት ሙያ አሁን ወዳለችበት ሕይወት መርቷት ለብዙዎች መፍትሄ እና ደጋፊ መሆንን ችላ በሀገሯ ውስጥ መኖርንን እንድትመርጥ አድርጓታል። ነኢማ ሙዘይን የይመለከተኛል የሱስ እና የአዕምሮ ህሙማን ማገገሚያ የበጎ አድራጎት ድርጅት መስራች ናት። በዛሬው እትማችንም የነኢማን ሕይወት ጉዞ እና ስኬት ለመቃኘት ወደድን፤ መልካም ንባብ።



ነኢማ ሙዘይን

### ልጅነትን በህብረት

ነኢማ ሙዘይን ተወልዳ ያደገችው በአዲስ አበባ ዘነበወርቅ አካባቢ ነው። አባቷ የጤና ባለሙያ ሲሆኑ እናቷ ደግሞ ጉሊት ሸጠው ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ ጠንካራ እናት ናቸው። ነኢማ ባደገችበት ቤት ውስጥ እሷን ጨምሮ ዘጠኝ ልጆች እህትና ወንድሞች አብረዋት አድገዋል። በዚህ ጊቢ ውስጥ ቤተሰባዊነት፣ እርስ በእርስ መረዳዳት ጎልቶ የሚታይበት የልጅነት ጊዜ መሆኑን ነኢማ ታስታውሳለች።

በልጅነት ጊዜዋ በትምህርቷ እምብዛም አልነበርኩም የምትለው ነኢማ በአባቷ እገዛ ትምህርቷ ላይ የነበራት ትኩረት መመለሱን አንስታለች። ዛሬ ላለችበት ደረጃ እና የሕይወት አስተሳሰብ ወላጆቿን ታመሰግናለች። አሁንም ድረስ በሃሳቧ እና በሕይወት ጉዞዋ የሚደግፏት እናቷን የምንጊዜም የሕይወት ጀግናዬ በማለት በምትጋበዝባቸው መድረኮች ላይ ሁሉ ታነሳቸዋለች።

የነኢማ ወላጅ እናት በአካባቢያቸው በነበራቸው እንቅስቃሴ እና ተሳትፎ የነኢማ ወደ ጋዜጠኝነት መሳብ እና ወደ ሙያው መግባት አጋጣሚም የእሳቸው መሆኑን ትጠቅሳለች። «ያኔ ልጅ ነበርኩ ከዚያ እናቴ በቀበሌ ውስጥ ይሰጥ የነበረ የጋዜጠኝነት ስልጠና እንድወስድ አደረገችኝ። እኔ ግን ስልጠናውን ከወሰድኩ በኋላ ብዙም ትኩረቴ አልነበረም። » በተማረችው የአጭር ጊዜ ስልጠና ነኢማ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ መሳተፍ እና ዝግጅቶችን ማቅረብ የመሳሰሉ ክህሎቶችን አዳብራ ነበር።

### ጉዞ ወደ አረብ ሀገር

ነኢማ ምንም ልጅ ብትሆንም በወቅቱ አቻዋ የሆነች እና አብራት የተማረች ጓደኛዋ ወደ አረብ ሀገር አቀናች። በምትኖርበት የአረብ ሀገርም ነኢማ ልትጓጓባቸው የምትችላቸውን ሁኔታዎች በፎቶግራፍ እያደረገች ትልክላት ጀመር። ነኢማ በፎቶ የምታየው የጓደኛዋ ሕይወት፤ ያለችበት ሁኔታ ይበልጥ አጓጓት። በዚህም ምክንያት ልክ እንደ ጓደኛዋ የሚያጓጓትን ሕይወት በአካል ማየት፤ መኖር እና ሰርታ መለወጥን ተመኘች። ተመኝታም አልቀረችም ወሰነች። ጉዞዋን ወደ አረብ ሀገር አደረገች፤ የተመኘችው በፎቶ የተመለከተችው ሕይወትና ነኢማ የገጠማት ግን በፍጹም የተለያየ ነበር። በየመን የቆየችበት ጊዜ መራር እና ፈታኝ ነበር። ነገር ግን ዛሬ ላይ ለደረሰችበት ብዙ የሕይወት ልምድን የወሰደችበት የተማረችበት ነበር።

ነኢማ ጓግታ የሄደችበት አስቸጋሪ የየመን ቆይታ ከሶስት ዓመታት በኋላ ትታ ወደ ሀገሯ ስትመለስ እናቷን ማሳረፍ እና መርዳት ፈለገች። በዚህም የጋዜጠኝነት ሙያዋን ወደ ተማረችበት ቀበሌ አመራች። በዚያም ንቁ ተሳትፎ የምታደርግ ወጣት ነበረች።

### በድጋሚ ከሀገር መውጣት

ነኢማ በሀገሯ ውስጥ ሕይወትን ለማሸነፍ ስትጥር ቆይታለች። በኋላ ላይ በትዳር አማካኝነት ወደ

**ነገር ግን በሥራዋ የሚደግፏት እና የሚያበረታቷት እንዳሉ ሁሉ ለምን አይቀርብሽም የሚሏት ብዙዎች ነበሩ፡፡ በምትኖርበት ሀገር ያላትን የሞቀ ሕይወት ትታ በመምጣቷ የሚቆጩ ሰዎችም በርካቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ አስተያየቶች ልባ ያልተበገረው ነኢማ የሀገሬ ጉዳይ የኔ ጉዳይ ነው በሚል ስያሜውን ‹‹ ይመለከተኛል የበጎ አድራጎት ድርጅት›› በሚል አዲስ ተቋም ለመመሥረት ቻለች**

አውስትራሊያ የሄደች እህት ነበረቻት። ይህች እህቷ የልጅ እናት ስትሆን ቤተሰቦቿ እንዲጎበኟት የሚያደርግ ግብዣ ላከችላቸው። በዚህ አጋጣሚ ነበር ነኢማ እንደገና ሌላኛውን የሰለጠነ ተብሎ የሚጠራውን ብዙዎች ሊሄዱ የሚመኙትን ሀገር ለማየት የቻለችው። በዚያ የተመለከተችው የባሕል ልዩነት እጅጉን አስፈራት። እሷ ከኖረችበት እና ከለመደችው ባሕል ጋር በፍጹም የተለያየ ሆነባት። በዚህ ወቅት ነኢማ በእምነቷ እየጠነከረች ወደ እምነቷ እየቀረበች መጣች። የሃይማኖት አባቶችን ትምህርትም መከታተል ጀመረች።

### እናትነት እና ኃላፊነት

ነኢማ የአንድ ልጅ እናት ናት። ታዲያ ልጅ በልጅነቱ ሲያዩት የሚያሳሳ፤ እድገቱ የሚጓጓ ነው። እያደገ እና የአፍላዎቹ እድሜ ላይ ሲደርስ ደግሞ አጉል ቦታ ላይ እንዳይወድቅ፤ በመጥፎ ምግባር ላይ እንዳይገኝ የሚያስጨንቅም ጭምር ነው። ልጇን በኢትዮጵያ ጥላ ወደ አውስትራሊያ የሄደችው ነኢማ የአንድ ልጇ ናፍቆት ስላላስቻላት ወደ እሷ እንዲመጣ አደረገችው። የልጇ ከእሷ ጋር መሆን መልካም ቢሆንም ሁኔታዎች ግን ለነኢማ ምቹ አልነበሩም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ እና በዚያ ሀገር ያለው የባሕል ልዩነት ልጇ ወዳልተፈለገ መንገድ እንዳያመራ አብዝታ ማብሰልሰል ጀመረች። ወጥቶ እስከሚገባ ድረስ መጨነቅ ሥራዋ ሆነ።

ነኢማ ለዚህም መፍትሔ ያደረገችው ልጇ እስኪያድግ እና ልብ እስከሚገዛ ድረስ በኢትዮጵያዊ ባሕል ታንጾ እንዲያድግ የሀገሩን ባሕል እንዲረዳ በመፈለግ ልጇን ይዛ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰች። ነገር ግን የልጇን ሕይወት ማስተካከል የተሻለ ማድረግ የማትደራደርበት ኃላፊነቷ ነበር። ልጇን በኢትዮጵያ አዳሪ ትምህርት ቤት አስገብታ በድጋሚ ወደ አውስትራሊያ ተመለሰች።

ነኢማ በአውስትራሊያ ቆይታለች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይም ሰርታለች። በቆየችበት የሥራ ዘርፍ ላይ በኢትዮጵያ እያለች የተማረችውን የጋዜጠኝነት ሙያ በአውስትራሊያ ቆይታዋ ልትሰራበት ችላለች። በዚያ የሚገኝ የኢስላሚክ የራዲዮ ጣቢያ ላይ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ትሰራ ነበር።

### በድጋሚ ወደ ሀገር መመለስ

በአውስትራሊያ በምትገኝበት ወቅት የኮቪድ 19 ወረርሽን ይፋ መሆን ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴዎችን ገደቡ። ይህ የእንቅስቃሴ ገደብ ቦታ እና ሁኔታ ያልለየው በመሆኑ እሷ በአውስትራሊያ መንሳቀስ በማትችልበት ሁኔታ፣ ልጇ ደግሞ ትምህርቱን አቋርጦ በቤት ውስጥ ለመቀመጥ ተገደዱ። በቤት ውስጥ ተቀምጦ መዋል ምቾት ያልሰጠው የነኢማ ልጅም እናቱ እንድትመጣ፣ አልያም እሱ እርሷ ወዳለችበት ለመሄድ እንደሚፈልግ ለእናቱ ደጋግሞ መናገሩን ቀጠለ። ነኢማም የልጇ ነገር አላስቻላትም እና በዚያ አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ ያሏትን ግንኙነቶች ተጠቅማ ከኮቪድ ወረርሽን ይፋ መደረግ ከስምንት ወር በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ መጣች።

### አዲስ መንገድ - በሀገር ቤት

ታዲያ የኮቪድ 19 ወረርሽን ይፋ በተደረገበት ሰዓት ልጇን ለማየት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ ስትመጣ ጊዜዋን እንዲሁ ማባከን አልፈለገችም። በአውስትራሊያ ቆይታዋ ትሰራው የነበረውን የጋዜጠኝነት ሥራ በኢትዮጵያም ማስቀጠል ፈለገች። የእስልምና እምነት ተከታዮች በብዛት የሚከታተሏቸውን የቴሌቭዥን ጣቢያዎች፤ የምታውቃቸውን ሰዎች በመጠቀም የራሷን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለመጀመር ወሰነች። የፕሮግራሙ ዋና አላማም በኖረችበት የሰለጠነ ዓለም ሰዎች የሚጓጉለትን «ሰለጠነ» የሚባለው ሕይወት ያለበትን ጉድለት ለማስተማር ፈለገች። ይህንኑ ለማስተማር የሚያስችላትን ቶክሾው ለማዘጋጀት ወሰነች። « ጄሉል ቲቪ » የተሰኘ ጣቢያ ላይ « ሹባክ ሾው» የቴሌቭዥን ፕሮግራምን ጀመረች ። በፕሮግራሙ ላይ የተለያዩ የእምነት አባቶችን በመጋበዝ ሀገራዊ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ፕሮግራሙን ለሰዎች ጠቃሚ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ማድረጓን ቀጠለች ።

### የአሳህ መንገድ

ነኢማ የቴሌቪዥን ፕሮግራሟ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ የቴሌቭዥን ፕሮግራሟን ከሚከታተሉ ሰዎች አንድ ልትሰራው የሚገባ ጥቆማ ደረሳት። ይህ አጋጣሚ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ለወገን የተከፈለ...

ከገጽ 6 የዞረ

የነኢማን ሕይወት ሙሉ ለሙሉ ቀየረው።

‹‹በከፍተኛ የትምህርት ተቋም በማዕረግ የተመረቁ ሁለት ወንድማማቾች አንድ ደግሞ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ እና በዚህ ሥራው ደግሞ ወንድሞቹን የሚያስተምር ወንድማቸው በአጠቃላይ ሶስት ወንድማማቾች በአዕምሮ ህመም ተጠቅተው የሱስ እስረኛ ሆነው የሚረዳቸው እንደሌለ እና ወጣቶቹ ለአስር ዓመት ያክል በሰንሰለት ታስረው ያለ አስታማሚ በቤት ውስጥ መኖራቸውን ሰማሁ። ›› የምትለው ነኢማ እነዚህ ሶስት ወንድማማቾች ሀድራ ሰኢድ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማዕረግ ተመራቂ፣ አብዱልቃድር ሰኢድ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የማዕረግ ተመራቂ በመሆን ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ናቸው። ሚፍታህ ሰኢድ ደግሞ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የቆየ ነው። ወንድማማቾቹ እናት እና አባታቸውን በሞት ተነጥቀዋል።

ነኢማ ይህ ከባድ ጉዳይ በፕሮግራሟ ለመሥራት ወጣቶቹ ወደሚገኙበት ገጠራማ ስፍራ በደቡብ ክልል ጉራጌ ውስጥ የምትገኝ ቸሀ ወረዳ አቀናች። ነኢማ ሁኔታውን እንዲህ ታስታውሰዋለች። ‹‹ለአስር ዓመት በነበረባቸው የአዕምሮ ህመም ማህበረሰቡ አግልሏቸው ቆይተው በቤት ውስጥ ታስረው ነው ያገኘኋቸው። ሆስፒታል ከመውሰድ ይልቅ ግን ሰዎች እንደ ጫትና ሲጋራ ያሉ ሱሶችን እየሰጡ የባሰ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ አድርገዋቸዋል። ›› ወጣቶቹ በሰንሰለት ታስረው የቆዩ ማህበረሰቡ አግልሏቸው እና ፈርቷቸው ያለ ቢሆንም ነኢማ ግን በሰላማዊ መንገድ ልታናነጋግራቸው ደፈረች።

ነኢማ የእነዚህን ወጣቶች ታሪክ ሰርታ ተመለሰች። ፕሮግራሙም በቴሌቪዥን መስኮት ተላልፎ ብዙዎች እንዲያዩት ተደረገ። እሷ ግን ከፕሮግራሙ መተላለፍ በኋላ እንዲሁ ዝም ብላ መቀመጥ አልቻለችም፤ ስሜቷ ሁሉ ስለእነዚህ ወንድማማቾች መጨነቅ ጀመረ። የውስጥቷን ፈተና ለመመለስ ወንድማቾቹ የሚያገግሙበትን ሁኔታ የጤና ተቋም፤ የማገገሚያ ማዕከል መፈለጓን ቀጠለች።

በዚህ አጋጣሚም ይረዱኛል ያለቻቸው ሆስፒታሎች ጋር በመሄድ እና የልጆቹን ሕይወት በተቀረጸው የተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየት የበርካቶቹን በር ማንኳኳት ጀመረች። የወንድማማቾቹን ታሪክ የተመለከቱ ሁለት የጤና ባለሙያዎች፤ ኢትዮ ጠቢብ ሆስፒታል እና ስጦታ ሆስፒታል ዶክተር ዮናስ ወጣቶቹን ለማከም እና የሚያርፉበትን ቦታ ለማመቻቸት ለነኢማ ቃል ገቡላት። ተገቢውን ህክምና እና ክትትል ካገኙም በቶሎ መዳን እንደሚችሉ አረጋገጡላት። ይህ ለነኢማ ትልቅ እረፍት ነበር።

ወንድማማቾቹ ወደሚገኙበት የቸሀ ወረዳ ተመልሳ ሄደች። ለአስር ዓመታት በሰንሰለት ታስረው የቆዩ ናቸውና እንዳያስቸግሯት በመፍራት ከወረዳው አስተዳዳሪ ጋር በመነጋገር የጸጥታ አካላት እንዲዘጋጁላት አደረገች። ነኢማ ግን እንደምትናገረው ‹‹ፈጣሪ የነገራቸው ይመስለኛል፤ ምንም ሳያስቸግሩኝ በሰንሰለትም ሳይታሰሩ ወደ አዲስ አበባ መጡ›› ስትል ጊዜውን ወደኋላ መለስ ብላ ታስታውሳለች።

ነኢማ የነበረችበትን አውስትራሊያ ጥላ ስትመጣ ልጇን ለማየት እና ከልጇ ጋር የተወሰነ ጊዜ ለመቆየት ነበር። ምክንያቱም የልጇ የሥነ ምግባር መሠረት በኢትዮጵያዊ ማንነት የታነጸ እንዲሆን ፈልጋለች እና። ታዲያ በድንገት ሳታስበው የገባችበት ሥራ ወደ አንድ ትልቅ የሕይወት ጥሪ አድርሷታል። የወንድማማቾቹን ታሪክ የተመለከቱ፤ ህክምና ካገኙ በኋላ ያላቸውን ለውጥ በሂደት ያዩ በርካታ እናቶች ተመሳሳይ የሆነ ችግርን ይዘው በቤታቸው የተቀመጡ ወላጆች ወደ ነኢማ ስልክ በተደጋጋሚ መደወል ጀመሩ። ነኢማ የምታስተናግዳቸው ስልኮች፤ የምትሰማቸው ታሪኮች ለአዕምሮዋ እጅግ ውጥረትን ፈጠሩባት። በዚህም የእናቶችን እንባና እረፍት ማጣት ሊቀንስ የሚችል መፍትሔም መፈለግም ቀጠለች። በተለያዩ የአዕምሮ ህመም የተጠቁ እና በተለያዩ ሱሶች ምክንያት ሥራቸውን መሥራት፤ የእለት ተዕለት ተግባራቸውን ማከናወን ያቃታቸውን ወጣቶች ለመርዳት ተነሳሳች። ብዙዎቹ በሱስ የተጠቁት ወጣቶች መሆናቸው፤ በይበልጥ ደግሞ በትምህርታቸውን በትልቅ ውጤት የተመረቁ ፤ ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ የተባሉ መሆናቸቸው የነኢማን ልብ ይበልጥ አስጨነቀው።

ታዲያ የምትሰራውን ሥራ መልካምነት በልጅነት አዕምሮው የተረዳው የነኢማ ልጅ እናቱ የጀመረችው ሥራ በሱ ምክንያት እንዳይሰናከል በማሰብ ወደ አውስትራሊያ ለመሄድ ወሰነ። እናቱም አደራውን ለአምላኳ ሰጥታ ልጇን ሸኘችው። እሷም የሀገሬ ጉዳይ ኃላፊነት አለብኝ ብላ እዚሁ ኢትዮጵያ ቀረች።

‹‹በጣም ብዙ እናቶች የተማሩ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ የደረሱ ልጆቻቸውን በዚህ ሱስ ምክንያት የአዕምሮ ህመም ተጠቂ ሆነው በቤት ውስጥ እንደታሰሩ፤ ወላጆች ወልደው የወላድ መካን እንደሆኑ እየደወሉ ይነግሩኛል። ›› የምትለው ነኢማ ከተለያዩ ቦታዎች የምትሰማውን የእናቶች ለቅሶ በፍጹም መቋቋም አልቻለችም። በሱስ ተጠቅተው የሚኖሩ ሰዎች ለህመማቸው መፍትሔ ያጡት በአብዛኛው በግንዛቤ እጥረት መሆኑን ተገነዘበች። ብዙዎች በህክምና መፍትሔ ከማግኘት ይልቅ ከሃይማኖታዊ ነገሮች ጋር በማገናኘት ጊዜያቸውን እንደሚፈጁ ተረዳች።

ታዲያ በእነዚህ ሶስት ወንድማማቾች ታሪክ ይመለከተኛል ያለችው ነኢማ መሰል ተመሳሳይ ታሪኮችን በብዛት በማስተናገዷ ተቋማዊ ለማድረግ ወሰነች።

ነገር ግን በሥራዋ የሚደግፏት እና የሚበረታቷት እንዳሉ ሁሉ ለምን አይቀርብሽም የሚሏት ብዙዎች ነበሩ። በምትኖርበት ሀገር ያላትን የሞቀ ሕይወት ትታ በመምጣቷ የሚቆጩ ሰዎችም በርካቶች ናቸው። በእነዚህ አስተያየቶች ልቧ ያልተበገረው ነኢማ የሀገሬ ጉዳይ የኔ ጉዳይ ነው በሚል ስያሜውን ‹‹ ይመለከተኛል የበጎ አድራጎት ድርጅት›› በሚል አዲስ ተቋም ለመመሥረት ቻለች።

## አዲስ ጉዞ

ነኢማ ኑሮዋን በአውስትራሊያ በአደረገችበት ወቅት ልትሰራቸው ያሰበቻቸው የራሷ ሃሳብ እና ህልም ነበራት። ነገር ግን በሀገሯ የተመለከተችውን ችግር እንቅልፍ የሚነሳ በመሆኑ ሃሳቦቿን ሁሉ እርግፍ አድርጋ ከፉውንም ደጉንም ከወገኗ ጋር ለመጋፈጥ ወሰነች። በሀገሯ ያየችውን ችግር ችላ ብላ ማለፍ፤ አይመለከተኝም ማለት አልቻለችም።

የበኩሏን አድርጋ ያየቻቸውን ችግሮች ለመቅረፍ በምትነሳበት ወቅት ብዙዎች ምን አገባሽ ፣ ለምን አትተይውም የሚል ጥያቄን ያቀርቡላት ነበር። ይህ ሃሳብ ያልተዋጠላት ነኢማ እኔ ይመለከተኛል፣ የአዕምሮ ህመም እናንተንም ይመለከታችኋል የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ላቋቋመችው ድርጅት ‹‹ይመለከተኛል ›› የሚል ስያሜ ሰጠችው።

ይህንን ሥራ ስትጀምር ሰዎችን የምታሳርፍበት ቦታ እጅግ አስፈላጊ ነበር። ነገር ግን ለዚህ ጉዳይ ብሎ የሚያከራይ ፍቃደኛ የሚሆን ሰው አጣች። ከዚያም ለሶስት ዓመት ያክል በኖረችበት ቤት ውስጥ እናቷን ወደ ሌላ መኖሪያ ቤት ቀይራ በራሷ መኖሪያ ቤት ውስጥ ሥራዋን ጀመረች።

የአእምሮ ህመምን በተመለከተ ሰዎች ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ የአዕምሮ ህመምን፣ ሱስን በቀላሉ መታከም የሚችሉ ህመሞች ቢሆኑም እጅግ ተባብሰው ሰዎች ራሳቸውን እስከ ማጥፋት ድረስ እንደሚደርሱ ነኢማ መገንዘብ ችላለች። በመሆኑም ሳይንሳዊ የሆነውን የህክምና ዘዴ ከመንፈሳዊ ህክምና ጋር በማጣመር ታካሚዎች ካለባቸው ችግር እንዲያገግሙ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካራ እንዲሆኑ ለሚያምኑበት እምነት ቅርብ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራን በዋናነት ትሰራለች።

## ከባድ ፈተናዎች

የአልኮሆል ሱስ ያለባቸው ተጠቂዎች ተጠቃሚ በነበሩት ጊዜ በቀን አንድ ጊዜ በልተው ሌላው ሰዓት ተጠቂ የሆኑበትን ሱስ በመጠቀም ይቆያሉ። ታዲያ ወደሱስ ማገገሚያ ማዕከል ከገቡ በኋላ ሙሉ በሙሉ ሱሳቸውን እንዲያቋርጡ ስለሚደረግ ወደማዕከሉ ከመጡ በኋላ ከባድ የሆነ ሳምንትን ያሳልፋሉ። ራሳቸውን እስከ ማጥፋት የሚያደርስ ሙከራንም ያደርጋሉ። ነኢማም ይህንን ሊከላከል የሚችል ክፍል ማቋቋም ነበረባት። ወጣቶቹ ሱሳቸውን በማቆማቸው ምክንያት በቀን ውስጥ የሚኖራቸው የምግብ ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ በየእለቱ መመገብ እንዲሁ ሌላው ተግባር ነው። ሆኖም ነኢማ ለዚህ ሁሉ ዝግጁ ባትሆንም በፈጣሪ እገዛ ችግሮቹን ተጋፍጣ ብዙዎችን እየረዳች ነው።

ነኢማ በሱስ ማገገሚያ ውስጥ ያሉ እነዚህ ወጣቶች እያገገሙ በሚሄዱበት ጊዜ እንዲያነቡ፣ ስፖርት እንዲሰሩ ታደርጋለች። በማዕከሉ ውስጥም ከተለያዩ ቦታዎች መንፈሳዊ እና ሌሎች መጽሐፎችን በመሰብሰብ በማዕከሉ ውስጥ ቤተ መጻሕፍት ገንብታለች። ነገር ግን በጫት ሱስ ውስጥ ወድቀው የቆዩ በመሆናቸው ያገኙትን መጽሐፍ ከማንበብ ይልቅ ቀዳደው የሚጥሉበት ጊዜ ብዙ ነው።

**ነኢማ በማዕከሉ ውስጥ ያሉ ታካሚዎችን ልጆቼ ብላ ትጠራቸዋለች ፡፡ ከሳምንት እስከ ሳምንት ይህ ነው የምትለው ፕሮግራም ወይንም ጉዳይ የላትም ፡፡ አብዛኛውን ጊዜዋን ከእነርሱ ጋር በማውራት ፣ እነርሱን ቀርቦ በማነጋገር ጊዜዋን ታሳልፋለች**

ነኢማ ይመለከተኛል የበጎ አድራጎት ድርጅት የአዕምሮ ህሙማን እና የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ስትመሰርት በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ነኢማ መምጣት ጀመሩ። ሆኖም የድርጅቱ አቅም እና የሰው ፍላጎት የሚመጣጠን አይደለም። ‹‹ማዕከሉ ገቢ የሚያገኝበት ወይም ድጋፍ የሚያደርግለት የለም። ›› የምትለው ነኢማ ችግሩን ለመፍታት በሁለት መንገድ ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ታካሚዎችን ታስተናግዳለች። አንደኛው አቅም ያላቸው ጥሩ የሆነ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወላጆች ልጆቻቸውን ይዘው ሲመጡ በማዕከሉ ያሉ ሌሎች ታካሚዎችን እንዲደግፉ ይደረጋል። አቅም የሌላቸው ወላጆች ሲመጡ ደግሞ ተመዝግበው በወረፋቸው ይስተናገዳሉ።

ነኢማ በማዕከሉ ውስጥ ያሉ ታካሚዎችን ልጆቼ ብላ ትጠራቸዋለች። ከሳምንት እስከ ሳምንት ይህ ነው የምትለው ፕሮግራም ወይንም ጉዳይ የላትም። አብዛኛውን ጊዜዋን ከእነርሱ ጋር በማውራት፣ እነርሱን ቀርቦ በማነጋገር ጊዜዋን ታሳልፋለች።

## ይመለከተኛል ዛሬ እና ነገ

ነኢማ ባቋቋመችው በይመለከተኛል የበጎ አድራጎት ድርጅት ውስጥ ከሚመጡ ታካሚዎች ውስጥ ቀላል በሆነ የድባቴ፣ በተለያዩ ሱሶች ውስጥ የእለት ተዕለት ተግባራቸውን ማከናወን ተስኗቸው፣ በቅርባቸው ሰዎች ርዳታ ማግኘት አቅቷቸው ወደ ሱስ ውስጥ የገቡ ወጣቶች በርካታ መሆናቸውን ትጠቅሳለች። በዚህም ርዳታ አግኝተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ መደበኛ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ሥራቸውን እንዲሰሩ ተደርጓል። ከተመሰረተ ሁለት ዓመት የሆነው የይመለከተኛል የበጎ አድራጎት ድርጅት የአዕምሮ ህመም እና የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ውስጥ ከ140 በላይ የሚሆኑ ታካሚዎች ይገኛሉ። እስከ አሁን በተሰራው ሥራም ከ500 በላይ የሚሆኑ ታካሚዎች ህክምናቸውን ጨርሰው እና አገግመው ከማዕከሉ ወጥተው ወደ ማህበረሰቡ በመቀላቀል የራሳቸውን ሕይወት መስርተዋል። በማዕከሉ የተሞሸሩም አሉ።

ሱስ እና የአዕምሮ ህመም ሰዎች ያላቸውን መደበኛ ሕይወት እንዳይመሩ ከማድረጉም ባሻገር ለወደቁለት ሱስ ተገዢ የሚያደርግ ነው። ታዲያ በማዕከሉ ውስጥ ካለባቸው ሱስ እና የአዕምሮ ህመም ለማገገም የገቡ ሰዎች /ታካሚዎች በየጊዜው የሚከታተሏቸው ሐኪሞች፣ የሥነ ልቦና ባለሙያዎች፣ የአካል ብቃት የሚሰሩ አሰልጣኞች የመንፈሳዊ ትምህርት አስተማሪዎች ይገኙበታል። የእነዚህ ሁሉ ውጤት የተሻለ ሰው እንደሚደርጋቸው ነኢማ ታምናለች።

ማዕከሉ በሙያዊ መንገድም ሆነ በገንዘብ የተለያየ እገዛ የሚያስፈልገው መሆኑን ጠቅሳ ብዙ ሰዎች ማዕከሉ ለማገዝ ቃል ቢገቡም የአዕምሮ ህመም እና ሱስ በመሆኑ ፈርተው የሚቀሩ እና የማይቀጥሉበት ሰዎች ይበዛሉ ስትል አሁንም ከአዕምሮ ህመም ጋር በተያያዘ ያለውን የግንዛቤ እጥረት ታነሳለች።

በአሁን ሰዓት የማዕከሉን ርዳታ ፈልገው ተመዝግበው ወረፋ የሚጠብቁ በርካታ ሰዎች ይገኛሉ። ታዲያ ነኢማ ይህንን ተቋም ማገዝ የሚችል እና ከማዕከሉ አገግመው ወጥተው ነገር ግን ሥራ በማጣታቸው ምክንያት ተመልሰው ወደ ሱስ ውስጥ የገቡ ወጣቶችን ለማገዝ የሚያስችል ወርክሾፕ በማቋቋም ላይ ትገኛለች። ‹‹ ተቋሙ በዋናነት የተመሰረተው ለድሆች አቅም ለሌላቸው ነው። ስለዚህ አገግመው ሲወጡ በዚህ ማዕከል ውስጥ የእንጨት ሥራ፣ ቴክኒሻን፣ የጸጉር ሥራ እና ሌሎች ሙያዎችን ተምረው ተቀጥረው የሚሰሩበትን እና ገቢ በማምጣት ተቋሙ ራሱን የሚደግፍበትን መንገድ እንፈጥራለን። ›› ስትል የማዕከሉን የነገ መንገድ ተልማለች።

# ባህልና ቱሪዝም

# የሚኒስቴሩንና የማህበራቱን በጋራ የመሥራት ፍላጎት ያመላከቱ መድረኮች

**ዳግም ከበደ**

በቅርቡ የቱሪዝም ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ የሥራ ርክክብ ካደረጉ በኋላ መደበኛ ሥራቸውን መጀመራቸው የሚኒስቴሩ የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ በይፋዊ የማህበራዊ ሚዲያ ገፆቹ አሳውቋል። ሚኒስትሯ ከሰሞኑ ደግሞ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ከሚሰሩ ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ ውይይት ማድረጋቸውንም ይሄው መረጃ ያመለክታል። ውይይቱ ዘርፉ የሚጠበቅበትን እድገት እንዲያመጣ ከሁሉም ባለድርሻ ጋር በቅንጅት መሥራት በሚችልባቸው እንዲሁም የማህበራቱና የባለድርሻ አካላቱ በሥራ ወቅት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመለየትና መፍትሔ ለመስጠት ያለመ መሆኑም ተጠቁሟል።

እንደ ሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ መግለጫ ከሚኒስትሯ ጋር ውይይት ካደረጉት ባለድርሻዎች መካከል የአስጎብኚ ማህበራት አንዱ ነው። በመድረኩም ማህበሩን ወክለው የተገኙ የሥራ ኃላፊዎች መንግሥት የቱሪዝም ዘርፉን ከዋና ዋና የኢኮኖሚው ዘርፎች ውስጥ እንዲካተት ከማድረግ ባሻገር አዳዲስ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎችን በማልማት እያከናወነ ያለው ተግባር ከምንጊዜውም በተለየ ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት እንደሚያሳይ አስታውቀዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሊያከናውናቸው ይገባል ባሏቸው፤ በተለይ ከክልሎች እና የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር የሚስተዋለው ቅንጅታዊ አሰራር ውስንነት፣ በመስህብ ስፍራዎች አካባቢ የሚስተዋሉ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች እና አገልግሎት አሰጣጥ መጓደል ያሉ ችግሮችን ማንሳታቸውን የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዓለማየሁ ጌታቸው ተናግረዋል፡፡

መረጃው እንዳመለከተው፣ ሚኒስትሯ የአስጎብኚ ማህበራት ኃላፊዎች እና ተወካዮችን ባወያዩበት ወቅት፤ ከቱሪዝም ኢንቨስትመንት፣ የመንግሥትና የሕዝብ ትብብር፣ በዓለም አቀፍና ቀጠናዊ ጥምረቶች፤ የንግድ ትርዒት እና ባዛሮች፤ በሀገራዊ የቱሪዝም መለያ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም ከቱሪዝም ገበያ ልማት አንጻር ከግሉ ዘርፍ ጋር መሥራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መወያየት ዘርፉ የተጣለበትን ሀገራዊ ፋይዳ እንዲያበረክት ወሳኝ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ከአሰራር ጋር በተያያዘ ከማህበራቱ አባላት በተነሱ ጉዳዮች ላይም ሚኒስትሯ በመሥሪያ ቤቱ በኩል መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር እንደሚከናወኑ መናገራቸውን ገልጸዋል። የዘርፉ ባላድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱም ሚኒስትሯ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

መረጃው እንደሚያመለክተው፤ የቱሪዝም ሚኒስትሯ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ምክክር ለማድረግ ከመረጧቸው ባለድርሻዎች መካከል የሆቴል ፌዴሬሽኖችና የቱሪዝም የሙያ ማህበራት ኃላፊዎች እንዲሁም ተወካዮች ይገኙበታል። ሁለቱም አካላት በዚህኛው መድረክ ላይ በቅንጅት መሥራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይም መክረዋል፡፡ በዚህም የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪው የዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን እና ተወዳዳሪ የሆነ አገልግሎቶችን እንዲያቀርብ መንግሥት አስቻይ የሆኑ የማበረታቻ ስልቶችን የዘረጋ መሆኑ የተጠቆመ ሲሆን፣ በጥምረት በመሥራት፤ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በመወያየት ዘርፉ የተጣለበትን ሀገራዊ ፋይዳ እንዲያበረክት ለማድረግ ወሳኝ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የማህበራቱ ተወካዮቹ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረትና የሳተላይት አካውንት ማስጀመሩን በማወደስ አሉብን ያሏቸውን ችግሮች ለሚኒስትሯ ማንሳታቸውን የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ ጠቅሷል፡፡ በተለይ ከሆቴል የኮኮብ ከደረጃ ምደባ አንጻር፣ ለእሳት አደጋ መከላከል የሚጠየቁ ፋሲሊቲዎችን በተመለከተ፣ የቀረጥ ነፃ የአንድ ጊዜ ፈቃድ ብቻ መሆን፤ በኮቪድ ምክንያት ገበያው የተቀዛቀዘው የሆቴል ኢንዱስትሪ በዳግም የደረጃ ምደባ ቁሳቁስ መቀየር ባለመቻላቸው ደረጃቸው ዝቅ ሊያደርግ ስለሚችል ከግምት ውስጥ ቢገባ የሚል እና የፋይናንስ አቅርቦት ችግር የተመለከቱ ጥያቄዎችን አንስተዋል።



የቱሪዝም ሚኒስትር ሰላማዊት ካሳ ከቱሪዝም ዘርፉ ባለድርሻዎች ጋር በተወያዩበት ወቅት

በተለይ ዘርፉ ችግር ላይ በወደቀበት ወቅት የ6 ወር እፎይታ ቢሰጥም አመርቂ አለመሆኑን፣ ከውጭ የሚመጡ ባለሙያዎች የቆይታ ጊዜ እና ያበቁት የሰው ኃይል እና ዓይነት የሚለይበት አግባብ መፍጠር ላይ ዘርዘር ያሉ ሃሳቦችን ማንሳታቸውን የሚኒስቴር መረጃው አመልክቷል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሳም ለባለድርሻ አካላቱ ወሳኝ ጥያቄዎች በቀጣዩ በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ የሚፈቱ ከሰው ኃይል ስልጠና አንጻር፣ ከትብብር እና ድጋፍ እንዲሁም የሚታዩ ክፍተቶችን በጋራ የሚፈቱበትን አግባብ እና የግንኙነት ጊዜ በተመለከተ አቅጣጫ ማስቀመጣቸውን ተገልጿል።

በተከታታይ ከተደረጉ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ውይይቶች መካከል ከሁነት አዘጋጆች ጋር የተካሄደው አንዱ ነው። ሚኒስትሯ በቱሪዝም ሚኒስቴር አዳራሽ በተካሄደው በዚህ ውይይት ላይ የትብብር እድሎች፣ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉ ተግዳሮቶች እና ኢትዮጵያን ዋና የማይስ መዳረሻ ለማድረግ በሚበጁ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ከአዘጋጆቹ ጋር መምከራቸውን የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ ገልጾልናል።

ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሳ የማይስ ኢንዱስትሪ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን መጥቀሳቸውን መረጃው ጠቁሞ፣ የዳበረ የኩነት ኢንዱስትሪ እንዲሆን መንግሥት ያለውን ቁርጠኝነት በአጽኖት ማስታወቃቸውን መረጃ አብራርቷል።

መረጃው እንደጠቆመው፤ የቱሪዝም ሚኒስቴር የኢትዮጵያን ገጽታ በዓለም አቀፍ ደረጃ መገንባት ዋና ሥራው በመሆኑ የዘርፉን እድገት የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና ወደ ተግባር እንዲገቡ በማድረግ ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆኑን ሚኒስትሯ ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻ መደበኛ የሆነ የግንኙነት አግባብ በመፍጠር አጋርነትን ማጎልበት እንደሚያስፈልግ መግለፃቸውን ጠቅሶ፣ የሁነት አዘጋጅ ድርጅት ተወካዮች በኢንዱስትሪው ፍላጎቶች ላይ ያላቸውን አጠቃላይ ግንዛቤ በማካፈል በአፍሪካም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ከመውጣት አንጻር በተግዳሮትነት የሚነሱ ጉዳዮችን ማንሳታቸውን አመልክቷል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትሯ ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ ባሕል እና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበራት እና የሀይኪንግ ኦርጋናይዘር አሶሴሽን ተወካዮች ጋርም እንዲሁ መክረዋል። ከእነዚህ ማህበራት ጋርም ሰፋ ያለ ጊዜ ወስደው መምከራቸውን የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ አስታውቆ፣ በውይይቱ ወቅት ማህበራቱ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ከሚጫወቱት ሚና ባሻገር እርስ በርስ መተዋወቅን በማስፋት ረገድ ቱሪዝም ለሀገራዊ አንድነት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያመጣ በአጽንኦት መግለጻቸውንም አብራርቷል፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ መሰል መድረኮች የእርስበርስ ትብብር መንፈስ የበለጠ እንደሚጨምሩ መናገራቸውን ጠቅሷል፡፡

በውይይቱ ላይ የተገኙት የማህበራቱ ተወካዮች ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት ሙያቸው በሚፈቅደው አግባብ አስተዋጽኦ እያደረጉ እንደሆነ ጠቅሰው፣ በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ከተቋሙ ጋር ተቀራርቦ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን መግለጻቸውን መረጃው ጠቁሟል። በዚህም ለሚፈለገውና ለተገቢው ውጤትም በጋራ ለመሥራት ፍቃደኛ መሆናቸውን ማሳወቃቸውንም ገልጿል።

የዝግጅት ክፍላችን በውይይቶቹ ላይ ከተሳተፉ ማህበራት መካከል የኢትዮጵያ የባሕልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት የሆነውን ተጓዥ ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩምን አነጋግሯል። ጋዜጠኛ ሄኖክ እንደሚለው፤ በውይይቱ ላይ ባለፉት 15 እና16 ዓመታት የባሕልና ቱሪዝም ጋዜጦች ክበብ፣ ፎረም እንዲሁም ማህበር በየደረጃው በማቋቋም ኢንዱስትሪውን ለማገዝ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በዝርዝር እንዳስረዱ ገልጿል። በተለይ የመገናኛ ብዙሃን እና የቱሪዝም ግንኙነት በቂ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ጠቅሶ፣ በተለያየ ቋንቋ ቱሪዝምን የሚመለከቱ ዘገባዎች አለመኖራቸውን የሚያሳዩ ውስንነቶች በመጥቀስ በቀጣይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ርምጃዎች የመፍትሔ ሃሳብ ማመላከታቸውን አስረድቷል።

ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም እነዚህን ተግዳሮቶች ለማለፍ የክህሎትና የአቅም ግንባታ እንዲሁም የፋይናንስ ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል፡፡ መንግሥትም ይህንንም ጉዳይ በተለይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንዲረዳው በምክክሩ ላይ ትኩረት በመስጠት ማቅረባቸውን ይናገራል።

የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ውጤታማ እንዲሆን በቀጣናው፣ በአህጉሪቱና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የቱሪዝም ሚዲያ ሊኖር እንደሚገባ መግባባት ላይ መደረሱን የማህበሩ ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ሄኖክ ይገልፃል። ይህንን ለማሳካት እስካሁን የተነፈገውን ትኩረት ማስተካከልና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለእቅዱ እውን መሆን አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባው መወያየታቸውንም ገልጾልናል።

‹‹ከዚህ ቀደም በዘርፉ ላይ በቅንጅት የመሥራት ባሕል ደካማ ነበር። በተለይ በፌዴራሉና በክልሎች መካከል ያለው ግንኙነት ላልቶ ነበር›› የሚለው የማህበሩ ፕሬዚዳንት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከክልሉ ቢሮዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖረውና በቅንጀት መሥራት እንደሚኖርበት ምክረ ሃሳብ ማንሳታቸውን ገልጿል።

እንደ ማህበሩ ፕሬዚዳንት ገለፃ፤ ሀገሪቱ የምትከተለው የአስጎብኚዎች ፍቃድ አሰጣጥ ሕግ (በተለይ ፍቃዱ የሚሰጠው መኪና ላሟላ ብቻ መሆኑን የሚገልጸው) ክፍተት እንዳለበትና መታረም እንደሚኖርበት በውይይቱ ተነስቷል። ይህ የፍቃድ አሰጣጥ ሕግ በኢንዱስትሪው ላይ ለመሥራት ፍላጎት የሌለውን ሰው መኪና ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ብቻ ምቹ አጋጣሚን እንዲያገኝ ክፍተት እንደሚፈጥር ማንሳታቸውን አስረድቷል። በዚህም ማህበራቱ የአስጎብኚነት ፈቃድ ሙያንና እውቀትን ገንዛቤ ውስጥ አስገብቶ መሰጠት እንዳለበት (መኪና ተከራይተው ሥራውን መሥራት የሚችሉበትን አማራጭም የሚጨምር) የሚገልፅ ሃሳብ ለሚኒስትሯ አቅርበዋል።

እንደ ማህበሩ ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ሄኖክ ሰዩም ፤ በውይይቱ ላይ የእግር ጉዞ ጉብኝት አዘጋጆች ማህበር የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማነቃቃት ላይ በርካታ ሥራዎች መሥራታቸውን ማንሳቱንም ይናገራል። በዚህም በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በየሳምንቱ ከአካባቢያቸው ራቅ ወዳሉ መዳረሻዎች እየወጡ ሀገራቸውን እንዲያውቁ ማድረጋቸውን ጠቅሶ የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እድገት እንዲመዘገብ በትብብር መሥራት አስፈላጊ መሆኑን መናገራቸውን ይገልፃል። ይህንን ወደ መሬት ለማውረድም ለሥራቸው የሕግ ማሕቀፍ ተዘጋጅቶ በፋይናንስና በፖሊሲ የሚደገፉበት እቅድ ተግባራዊ እንዲደረግ ለሚኒስትሯ ጥያቄ አቅርበዋል።

‹‹ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለድርሻ አካላትን በተናጠል ጠርቶ በዚህ መልኩ ካወያየ ረጅም ጊዜ ሆኖታል›› የሚለው የማህበሩ ፕሬዚዳንት፤ ከዚህ ቀደም የባለድርሻ አካላቱን ችግርና በጋራ አብሮ ለመሥራት የሚገድብ እንቅፋት እንደነበር አስታውሶ፣ መንስኤው ምን ነበር ተብሎ ተጠይቆ እንደማያውቅ ይናገራል። አሁን በዚህ መልኩ እድል መሰጠቱና የጋራና የትብብር ሥራዎችን በቅንጅት ለመሥራት የተጀመረው ጥረት ሊደነቅ የሚገባው በጎ ጀምር መሆኑንም ያነሳል።

ይህንን ለማላቅ የኢትዮጵያ የባሕልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር ሌሎች ማህበራትን በማስተባበር አንድ ማሕቀፍ ለመፍጠር እየሰራ መሆኑን ገልጿል። ይህንን ስኬታማ ማድረግ ከተቻለ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቅንጅት ለመሥራት መድረኮችን ክፍት ከማድረጉ ጋር ተደምሮ በኢንዱስትሪው ተስፋ ሰጪ ውጤት በቅርቡ እንደሚመዘገብ አስረድቷል።

# ሳምንቱን በታሪክ

# ባለ ገድሏ ሸዋረገድ ገድሌ

**ዋለልኝ አየለ**

በታሪክ ውስጥ የአርበኝነት ተጋድሎ ሰፊ ቦታ አለው፤ ምክንያቱም የሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው። አርበኝነት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆኖ የሚጠቀሰው ደግሞ አፍሪካ ውስጥ ሆና ቅኝ ያልተገዛች ነፃ ሀገር መሆኗ ነው። አንዲት አፍሪካዊት ሀገር የአውሮፓን ቅኝ ገዥ በዱር በገደል ተዋግታ ነፃነቷን ስታስጠብቅ ዓለም አቀፍ ገድል መሆኑ ግልጽ ነው። እነሆ እነዚህን አርበኞቻችንን ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ብዙም ባልተነገረውና ባልተዘመረው የሴቶች የአርበኝነት ተጋድሎ ውስጥ ነጥረው የወጡትን አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌን እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ታሪካዊ ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ120 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 19 ቀን 1897 ዓ.ም ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪ፣ የግብርና ሳይንስ ሊቅ፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና ፖለቲከኛ የነበሩት ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል ተወለዱ።

ከ94 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 22 ቀን 1923 ዓ.ም ፒያሳ (አራዳ ጊዮርጊስ) የሚገኘው የዳግማዊ አጼ ምኒልክ መታሰቢያ ሀውልት (ምኒልክ አደባባይ) ተመረቀ። ይህ የሆነው በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የንግሥና በዓል ዋዜማ ነበር። በዚሁ ዓመት ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሆነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ።

ከ108 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 23 ቀን 1909 ዓ.ም ደራሲ፣ መምህር፣ ባለቅኔ፣ ፀሐፌ ተውኔት፣ ፖለቲከኛ፣ ገጣሚ ... የክብር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ተወለዱ።

ከ60 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 23 ቀን 1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ኢቲቪ) ስርጭቱን ጀመረ። ይህ ብሔራዊ ቴሌቭዥን እነሆ በዚህ ዓመት 60ኛ ዓመት ሆነው።

ከ55 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 24 ቀን 1962 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው አንጋፋው ሒልተን ሆቴል ሥራው ተጠናቆ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ተመረቀ። የሆቴሉ ዲዛይን የተሰራው በአንድ የአሜሪካ ሥነ ሕንጻ (አርክቴክት) ድርጅት ሲሆን፤ ሆቴሉ ተቀማጭነታቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉ ዲፕሎማቶች ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣትን ተከትሎ የተገነባሠየቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ፕሮጀክት ነው።

ከ117 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 25 ቀን 1900 ዓ.ም ፒያሳ የሚገኘው ታሪካዊው የጣይቱ ሆቴል ግንባታው ተጠናቆ ተመረቀ።

በዝርዝር ወደምናየው የአርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ገድል ስናልፍ፤ ከ75 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 22 ቀን 1942 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በአርበኝነት ተጋድሎ ዘመን የማይሸረው አኩሪ ገድል ከፈፀሙት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዷ የነበሩት ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ አረፉ።

የዓድዋ ሽንፈቷን ለመበቀል ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረረች። የኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም አንዲትም ቀን እንኳን እፎይ ብሎ ሳይቀመጥ ከአምስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሌላ የሽንፈት ማቅ ለብሶ ከኢትዮጵያ ምድር ተባረረ። ታዲያ በዚህ አስገራሚና አኩሪ የመስዋዕትነት ጉዞ ውስጥ ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ከፃፉና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ከተጋደሉ እልፍ የኢትዮጵያ ጀግኖች መካከል አንዷ ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ነበሩ።

አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የተወለዱት በ1878 ዓ.ም ደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ ነው። የቤተ ክህነት ትምህርት ተምረዋል። ለአቅመ ሔዋን ሲደርሱ ያገቧቸው ባል ብዙም ሳይቆዩ ስለሞቱባቸው ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው ተቀምጠው ቆይተዋል።

በ1888 ዓ.ም በጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ድል የሆነው የኢጣሊያ ጦር ቂሙን ሳይረሳ ሽንፈቱን ሳይዘነጋ ከአርባ ዓመታት በኋላ ዳግመኛ ለብቀላ በተመለሰበት አጋጣሚ በአዲስ አበባ ከተማ በሀገር ተቆርቋሪ ዜጎች መስራችነት «የሀገር ፍቅር ማህበር» ተቋቋመ። በማህበሩ በአባልነት ለመጀመሪያ ጊዜ ከተመዘገቡ ሴቶች መካከልም ጀግናዋ ሸዋረገድ ገድሌ አንዷና ግንባር ቀደም ነበሩ።

ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ሀገራችንን እንደገባ የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው ለዘመናት በድል ሲውለበለብ የቆየውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በማውረድ የራሱን ባንዲራ መተካትን ነበር።

በወቅቱ ይህን ድርጊት በዓይናቸው የተመለከቱት ሸዋረገድ ግን ወራሪውን ጦር ሳይፈሩና ሳይሳቀቁ «ሀገሬ ተወረረች፤ ተዋረደችም» ሲሉ አምርረውና ጮኸው ማልቀሳቸውን ተያያዙት። ሁኔታቸውን ያዩ የጣሊያን ሹማምንትም የእርሳቸውን ድርጊት እንደ ድፍረት በመቁጠር ለክስ አቀረቧቸው። ሸዋረገድ ግን በተለየ ወኔ ተሞልተው «አዎ አልቅሻለሁ! የሀገሬን መወረርና መዋረድ ያወቅሁት የኛ ሰንደቅ አላማ ወርዶ የእናንተ ሲወለበለብ በማየቴ ነው። ሰው ለእናት ሀገሩ ቢያለቅስ ነውሩ የቱ ላይ ነው?!» ሲሉ እልህ በተሞላበት ሁኔታ መለሱላቸው።

ሸዋረገድ ሀገራቸው በጠላት ጦር ዳግመኛ መወረሯ ከታወቀ ወዲህ «ሕይወቴ ሀገሬ ናት» ሲሉ ለመታገል ቆረጡ። ከወራሪው የጠላት ጦር ጋር ሊፋለምና ደሙን ለሀገሩ ሊገብር ለተዘጋጀው ወገን ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ትጥቅ እያደራጁና ስንቅ እያዘጋጁ እንዲሁም ከኢትዮጵያውያን ሴቶችም ቁርጥራጭ ጨርቆችን እያሰባሰቡ በጦርነቱ ለሚጎዱ ቁስለኞች እንዲላክ ያደርጉና ይሰጡ ጀመር።

የእሳቸው ድርጊት ግን ለኢጣሊያኖቹ ሰላም አልሰጠም። ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት አልፈው ለክስ እንዲቀርቡ ወሰኑባቸው። ወይዘሮ ሸዋረገድ ለአርበኞች ስንቅ በማቀበላቸው፣ መሣሪያ በመግዛታቸው፣ መረጃ በማሰባሰባቸው፣ መድኃኒት በመላካቸውና ሞራል በመስጠታቸው ምክንያት በተከሰሱ ጊዜም ‹‹ለአርበኞች ስንቅ ማቀበሌ እውነት ነው፤ ይህንንም ያደረግኩት ለሀገሬ ክብር ብዬ ነው። ሰው እንኳን ለሀገሩ ... የእናንተ ወይዛዝርት ሀገራቸው ያልሆነቺው ኢትዮጵያን ለመውረር የጣታቸውን ቀለበት ሳይቀር መስጠታቸውን ትናገራላችሁ። እኔም ለሀገሬ የሠራሁት ሲያንሰኝ እንጂ አይበዛብኝም!›› በማለት ስለፈፀሙት ድርጊት ሁሉ ኩራት እንደሚሰማቸውና ይህንንም ያደረጉት ለሀገራቸው ክብር ሲሉ እንደሆነ በድፍረት ተናገሩ።

አርበኛ ሸዋረገድ ከሚጠቀሱላቸው ሥራዎቻቸው አንዱ ለቀይ መስቀል ማህበር ያደርጉት የነበረው ድጋፍ ነው። በጦርነቱ ዋዜማ፣ በ1927 ዓ.ም ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ንብረታቸውን ሸጠው በማስረከብ ሀገር ወዳድነታቸውን አስከብረዋል። ከተከሰሱባቸውና ‹‹ወንጀል›› ተደርገው ከተቆጠሩባቸው ድርጊቶች መካከል አንዱ ይኸው ለቀይ መስቀል ያደርጉት የነበረው ድጋፍ ነው። እሥር ቤት በገቡ ጊዜም የፋሺስት አስተዳደር ባለሥልጣናት ‹‹ቀይ መስቀልንና ሀገር ፍቅር ማህበርን ትረጃለሽ›› ብለው ክስ አቅርበውባቸው ነበር። የጠላቶቻቸውን ክስ ከቁብ ያልቆጠሩት አርበኛ ሸዋረገድ ግን ‹‹ስለ ነፃነት ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው የሌሊት ቁርና የቀን ሐሩር ከሚገርፋቸው የሀገሬ አርበኞች ጎን ተሰልፌ ጠላቴን መውጋቴ ቀርቶ የረሃብና የጥም መድኃኒት እያዘጋጀሁ መላኬ ቁም ነገር ሆኖ ነው የተጠየቅሁበት? እኔ ይህን ባለማድረጌና ለሀገርም ባልቆረቆር፤ እንኳን እነሱ እናንተም እንደምትታዘቡኝ ይሰማኛል›› በማለት እጅግ አስደናቂ የሆነ የሀገር ፍቅር የተሞላበትና ቆራጥነት የተቀላቀለበት መልስ ሰጥተዋል።

አርበኛ ሸዋረገድ ከቁሳቁስ ርዳታው ጎን ለጎን ለአርበኞቹ የመረጃ ምንጭም ነበሩ። በከተማው የሚገኙ የጠላት መረጃዎችን በማሰባሰብና ወደ አርበኞች በምሥጢር በመላክ አርበኞች እንዲጠቀሙባቸው አድርገዋል። ይህ ተግባራቸውም ከወቅቱ ‹‹የውስጥ



አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ

አርበኞች›› መካከል አንዷና ዋነኛዋ ሆነው እንዲቆጠሩ አስችሏቸዋል። ሸዋረገድ ለኢጣሊያ ሰዎች ወዳጅ በመምሰል ለኢትዮጵያውያን አርበኞች መረጃ ይሰጡ ስለነበር የኢጣሊያ ፋሺስቶች ሸዋረገድ እውነተኛ ወዳጃቸው መስለዋቸው ‹‹አርበኞችን ከረዳሽ እኛን አትወጂንም ማለት ነው?›› ብለው ሲጠይቋቸው ‹‹አዎ አልወዳችሁም! ማነው የሀገሩን ደመኛ የሚወደው?›› በማለት ቁርጥ ያለ ምላሽ ሰጥተዋቸዋል።

አርበኛዋ ሸዋረገድ በሚፈፅሟቸው በርካታ ፀረ ፋሺስት እንቅስቃሴዎች ምክንያት ጥርስ የነከሱባቸው የፋሺስት ኢጣሊያ አስተዳደር ባለሥልጣናት ሕይወታቸውን በእስር እንዲገፉና ቆይቶም ሞት እንዲፈረድባቸው ወስነው ነበር። ሆኖም አዚናራ ወደምትባልና በሰሜናዊ ምዕራብ ኢጣሊያ ወደምትገኝ ደሴት ታስረው እንዲቆዩ ከተደረገ በኋላ ፍርዱ ወደ እስራት ብቻ በመቀየሩ ምክንያት የእስር ዘመናቸውን በደሴቲቱ እንዲገፉ ተወሰነባቸው።

ጀግናዋ አርበኛ ሸዋረገድ ግን የቦታ ለውጥና ርቀት አልበገራቸውም። በጠላት ሀገር ሆነውም ጽናታቸው አልተሰበረም፤ ወኔያቸውም አልተሰለበም። እንዲያውም ወኔያቸውን አጠናክረው ትግላቸውን ቀጠሉ። በእስር ቤቱ የሚቀርብላቸውን ምግብ በአሳሪዎቻቸው ፊት በመድፋትና ጦማቸውን ውለው በማደርም ተቃውሞ ማድረግ ጀመሩ። ከአንድ ዓመት የእስራት ቆይታ በኋላ ከእስራት እንዲለቀቁ በመወሰኑም ወደ አዲስ አበባ የመግባት እድል አገኙ። በወቅቱ ወደ አዲስ አበባ ሲገቡም ሕዝቡ ...

« የዘበኛ ሱሪ ካኪና ገምባሌ፣
እንኳን ደህና መጣሽ ሸዋረገድ ገድሌ »

ብሎ በመግጠም ተቀበላቸው። በተለይ በጅቡቲ የነበረ አንድ ኢትዮጵያዊ የሰጣቸውን ‹‹የይሁዳ አንበሳ›› የሚል ጽሑፍና ዓርማ ያለበትን ወረቀት ከንጉሰ ነገሥቱ የተላከ የሚመስል መልዕክት እየፃፉ አርበኞች ተጋድሎ ወደሚያደርጉባቸው ልዩ ልዩ ስፍራዎች በመላክ አርበኞቹ እንዲበረታቱ አድርገውበታል።

አዲስ ዓለም አካባቢ ይገኝ የነበረው የፋሺስት አጣሊያ ምሽግ ኅዳር 5 ቀን 1933 ዓ.ም ሲሰበር ጠቃሚ መረጃዎችን ለአርበኞች በማሰባሰብና በርካታ እቅዶችን በመንደፍ ታላቁን ድርሻ የተወጡት ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ነበሩ። ምሽጉ ከተሰበረም በኋላ ደጀን መሆኑን ትተው ወደ ውጊያ ለመግባት በመወሰናቸው ከሻለቃ በቀለ ወያ ጦር ጋር ተሰልፈው ጠላትን ተፋልመዋል። በመቀጠልም ወደ ወሊሶ በመሄድ ከደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጦር ጋር ሆነው ተዋግተዋል። በጦርነቱ የአራት ሰዓታት ውጊያ ላይ ጠላት በጣለው ድንገተኛ አደጋ ከታላቅ ተጋድሎ በኋላ የተማረኩት አርበኛ ሸዋረገድ፣ በድጋሚ በፋሺስት ኢጣሊያ ወታደሮች እጅ በመውደቃቸው የፊጥኝ ታስረው ወደ እስር ቤት ተወረወሩ። የሸዋረገድን ጀግንነት የተመለከተው ሕዝብም ...

« የምታስፎክር ሰንጋ ገለሌ፣
በጦር መካከል ሳይሆኑ አያሌ፣
በጥይት ገዳይ ነጭ ብር ገድሌ፣
የሴት ወንድ ናት ሸዋረገድ ገድሌ »

ብሎ ጀግንነታቸውን በማድነቅ አወድሷቸዋል። የጀግኖች አርበኞች ትግል ተጠናክሮ የጠላት ጦር በመጣበት እግሩ በታላቅ ውርደትና በአሳፋሪ ሽንፈት በ1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲባረር ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌም ነፃ ሆነው ተፈቱ። ከዚህ በኋላ ሕይወትን በነፃነት ማጣጣም ለእኚህ ታላቅ ሴት ትልቅ ትርጉም ነበረው። ቀድሞ የጀመሩትን አርበኞችን የመርዳት የበጎ አድራጎት ሥራቸውን አጠናክረው ቀጠሉበት። በንግዱ ዘርፍ ተሰማርተውም በርካታ ሰዎችን እንደጠቀሙም ይነገርላቸዋል።

ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ታዋቂ ያደረጋቸው የአርበኝነት ሥራቸው ሆነ እንጂ ከመጀመሪያዎቹ የባንክ ተጠቃሚዎች፣ የአክስዮን ገዥዎች፣ የፋብሪካ ተካፋዮች መካከል አንዷ ነበሩ። በእነዚህ የንግድ ሥራዎቻቸውም በርካታ ሰዎችን በተለይ ደግሞ ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻሉ ታሪካቸው ያስረዳል። በሃይማኖታቸውም ጠንካራ እንደነበሩ ታሪካቸው የሚናገረው አርበኛዋ፣ የጉለሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንንም ያስተከሉት እርሳቸው ናቸው።

ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ለወቅቱ አርበኞች በመሳሪያ፣ በስንቅና በመረጃ ያደርጉላቸው ከነበረው ድጋፍ በተጨማሪ ከአንዳንዶቹ ጋር በጦር ሜዳ አብረው ተሰልፈው ተዋግተዋል። ለአብነት ያህልም ከጀግኖቹ አርበኞች ደጃዝማች በቀለ ወያ እና ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጋር ተሰልፈው ከጠላት ጦር ጋር ተፋልመዋል። ለታዋቂው አርበኛ ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎም ልዩ አክብሮት ነበራቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ሊጠቀስ የሚገባው አንድ አጋጣሚ አለ።

ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከእንግሊዝ ተመልሰው ዙፋናቸው ላይ ቢቀመጡም ጎንደርና ጅማ ከጠላት ጦር አልተለቀቁም ነበር። ‹‹መጀመሪያ የቅርቡን እናስለቅቅ›› ተብሎ ወደ ጅማ ሲሄዱ የፋሺስት ጦር የጊቤን ድልድይ ቆርጦ መከላከል ጀመረ። በዚህ ጊዜ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጃገማን ያውቋቸው ነበርና ለንጉሠ ነገሥቱ ‹‹ለጃገማ ትዕዛዝ ቢሰጡልኝ በአምቦ መንገድ ሄዶ በኋላ በኩል ይቆርጥልኛል›› በማለታቸው ጃገማ ከደጃዝማችች ገረሱ ጋር እንዲዘምቱ በደብዳቤ ታዘዙ።

አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ለንጉሠ ነገሥቱ ‹‹ጃንሆይ ይህ ልጅ ገና ሕፃንና የሚያምር ልጅ ነው፤ እንዴት ከሞት ወደ ሞት ይልኩታል? ያሰናብቱት! ጦሩን ቢያዩለትም መልካም ነው›› ብለው ስለተናገሩ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ‹‹እውነት ነው፤ ተሣሥተናል፤ እናያለን፤ ጦርህን መጥተን እናያለን ተዘጋጅተህ ጠብቅ፤ ፉከራም ታሰማለህ›› ብለው አዘዙ። ንጉሠ ነገሥቱም የጀግናውን ጦር ጎብኝተው ከጃገማ ጋር ምሳ በሉ። ከዚያም ጃገማ አዲስ አበባ መጥተው ከንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሽልማት (25ሺ ብር፣ የወርቅ ሰዓት እና ሙሉ ገበርዲን ሱፍ) ተቀበሉ። ከዚያም ጃገማ ወደ ደጃዝማች ገረሱ ዘንድ ዘምተውና የለመዱትን ጀብድ ፈፅመው በቦታው የነበረውን የፋሺስት ጦር ዋና አዛዥና ሌሎች መኮንኖችን ማርከው ጦርነቱንም በድል ፈጸሙ።

በመጨረሻም ግሼን ማርያም ሄደው ሥጋ ወደሙን ተቀብለው፤ ከዚያም ወደ ላሊበላ ተጉዘውና ተሳልመው፤ የመጨረሻቸው መሆኑን እየተናገሩ ጥቅምት 22 ቀን 1942 ዓም አረፉ። የአርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የመሞታቸው ዜና እንደተሰማ ሕዝቡ እንዲህ ብሎ አንጎራጉሮላቸው ነበር።

« እናንት ወጥ ቤቶች በርበሬ ቀንጥሱ፣
እናንት ሥጋ ቤቶች ሰንጋውን ምረጡ፣
ሸዋረገድ ገድሌ ለገና ሲመጡ።
ቤተሰቧ ሰፊ ገናና ጥምቀት፣
ሸዋረገድ ገድሌ እንደምን ትሙት። »

ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የአብራካቸው ክፋይ የሆነ ልጅ አላፈሩም። የልጅ መካን ቢሆኑም የአኩሪ ታሪክ እናት በመሆናቸው ስማቸው በጀግንነት ሕያው ሆኖ እነሆ ሲዘከር ይኖራል።

# የዝነኞች ገጽ

# የእሳት ዳር ፍሬ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ነገን በተስፋ ርቀት እየተመለከቱ ድንገት ቦግ እልም! ጭልምልም! ያለ ዕለት የከፋ ነው። ያማል። በቁስል የተመታ ልብ ይደማል። ያመኑት ፈረስ ሲከዳ ከፍ ብሎ ዝቅ እንደማለት የሚከብድ ነገርም የለም። የማይባረድ የኑሮ እሳት ወላፈን እየለበለበ ያረረውን ጨለማ ያስመለከተ ዕለት ቀቢጽ ተስፋ ይጠፋል። የወንዝ ዳር ፍሬ ከጅረቱ ልምላሜን የለመደ እንደምንስ ብሎ ከእሳት ዳር ለመኖር ያስችለዋል? በነበልባሉ ወላፈን እየተቃጠሉ፣ ከፊት የሚጠጋውን እሳት ከመመልከት በላይ ሲቃ የለም። ዘር ታቅፋ ዛፍ ለመሆን የምትሻ ፍሬ ለቅሶዋ ለዛፉም ጭምር ነው። ሞቷም የትልቁ የተስፋ ዛፍ ሞት ነው።

ትናንትና ከለምለም መስክ ላይ ያረፈችውን የሕይወት ፍሬውን ተመልክቶ "ስንት አየሁ ሲሳይ" ስለማለት ሲያስብ ሲያሰላስል ነበር። አዱኛውን ሰብስቦ፣ ሲሳዩን ለመቅመስ ፈገግ ብሎ በሀሴት እያጌጠ ነበር። ሕይወት ሙሉ ሙሉ፣ ኑሮም የተድላ ፍስሀ ነበር። እያደር ሁሉም እየቀረ እንደ ፀሐይ ስታሞቀው የነበረችው ሕይወትም እንደ ሀሩር ንዳድ ታነደው ጀመር። በሥራዎቻቸው የምንዘምርላቸው ታላላቅ የጥበብ ልጆች በየእሳት ገደሉ እየሰጠሙ ካለፈ ወዲያ መላቀስ ለኛ አዲስ አይደለም። የወደፊቱን ባናውቅም ከበፊቱም የነበረ ያለ ነው። ወላዷ ጥበብ ደረቷን ስትደቃ መመልከት ለኛ ትርኢት ሆኗል። ግን እስከመቼስ ነው መሽቶ በነጋ ቁጥር ሁሉ ስናላዝን የምንኖረው?

በየኑሮ ኤርታሌው ስለሚወድቁት ከትናንት ጳጳታችን ለመማር እኮ ሁሉም ታጭደው እስኪያልቁ መጠበቅ አይኖርብንም፤ ካቃተን ለዓመት ሁለት ሦስቱ በቂ ነበሩ። የዘንድሮውም ሰሞነኛ የባሰውን አሰማን። ብዙዎች አምቀውና ታምቀው በዚያው ሲቀሩ እርሱ ግን ከሚዲያ አደባባይ ላይ ወጥቶ ድረሱልኝ ማለቱ አስደንጋጭ ነበር። የተዳረስንበትን የመረሳሳት ጥግ የሚያሳይም ጭምር። ጩኸቱ የአንድ የስንታየሁ ሲሳይ ቢመስልም በውስጡ የብዙዎቹን የሚያሳይ መስታወት ነው። ኑሮ የከፋ ዕለት የሀፍረትን ማቅ ለብሶ፣ ይሉኝታን በጣጥሶ አደባባይ እንደመውጣት ያለ ረመጥ የለም። ግን ይሄ የጥበብ ፍሬ አደረገው። ወጣ።

ከዛሬው የእሳት ዳር ጩኸት፣ አስቀድሞ ከነበረበት የወንዝ ዳር ፍሬነት እንጀምረውና የዝነኛውን አጥር ወደኋላ እንዝለለው። ዓይን ሳንነቅል፣ ልብ ተክለን የተመለከትናቸውና ያደመጥናቸውን ምርጥ ምርጥ የሙዚቃ ክሊፖችን ያበረከተልን ስንታየሁ ሲሳይ ሥራውን ለትርፍና ጥቅም ሲል እንዳያሳልጥ ያደረገው ነገር፤ በልጅነት ካደገበት ማህበረሰብ የሕይወት ዘዬ በመቀዳቱ እንደሆን ይናገራል። ጭንቁ ሥራው ነበር። ስንታየሁ የት ተውልዶ ቢያድግ ይሆን ከዚህ ማንነት መቀዳቱ? ... ፍቅር እንጂ ጥላቻ፣ ሰው እንጂ ዘር፣ መተሳሰብ እንጂ ጭንቀት፣ መስጠት እንጂ ንፍገት ከማይታወቅባት የልደታ ሰፈር ውስጥ ነበር ተወልዶ ያደገው። "ከጎረቤት በዳንቴል ተሸፍኖ ከሚቀባበል ማህበረሰብ ነው ያደግኩት" ይላል።

ልጅ ሆኖ ወላጅ እናቱ ዳዊት እንዲደግም ቤተክርስቲያን፣ ቁርአን እንዲቀራ መስጊድ አስገብታው እንደነበረ አይዘነጋውም። ወዲህ በቅዳሴ፣ ወዲያ በአዛን ተኮርኩሯል። እንዳደገበት ማህበረሰብ በነበሩ አካባቢዎች ሁሉ ይኼ የብዙዎች ታሪክ ነው። ኢትዮጵያዊነት በአካለ ሰው ተገልጦ የሚታይበት ነበር፤ ነበር ከማለታችን አስቀድሞ። በእነርሱ ውስጥ ራስን ወዶ፣ ከራስ ተፋቅሮ ወርቅ ቁፋሮ አይገባምና እርሱም ጥቅሙን አስልቶ የሚሰራ አልሆነም። "ለገንዘብ ስል ሠርቼ አላውቅም። ስለራሴና ስለቤተሰቤ እንኳን ሳልጨነቅ የወደድኩትን ሥራ ነው የምሠራው። ኢትዮጵያዊነት የሚታይበትና ዛሬ ላይ ልጆቼ ሲያዩት የማያፍሩበትን ሥራ ነበር የምሠራው። እነዚያ ነገሮች ጋር ዋጋ አስከፍለውኛል" ሲል ባንደበቱ ተናግሯል። ባይሆንማ ኖሮ እኚያን ሁሉ የሙዚቃ



ስንታየሁ ሲሳይ

ክሊፖችን የሠራ፣ በአድናቆት ያጨበጨብንለት ሰው ዛሬ "ለልጆቹ መሆን ተሳነኝ" ሲል ባለሰማን ነበር።

ጎልማሳው ስንታየሁ ሲሳይ ቀደም ሲል የወጣትነቱን ገሚስ ያሳለፈው በጥበብ ሳይሆን በእግር ኳስ ሜዳ ላይ ነበር። ለኳስ ካደለው ተክለ ሰውነቱና ችሎታው ጋር ነገን ለሀገሩ የሚመኙለት ነበር። ወደ ታችኛው የአሜዱላ እግር ኳስ ቡድን ተቀላቅሎ በ"ሲ" ቡድን ውስጥ 3 ወራት ያህል ከሰለጠነ በኋላ ወደ "ቢ" ከፍ አለ። ከአሰልጣኙ ንጉሴ ገብሬ ጋር ለኳስ ትዕይንት ሲሰናዳ ድንገት ግን ዋናውን ቡድን ሳይቀላቀል ጥበብ ጠራችው። ከኳስ ሕይወቱ ባሻገር ወደ ጥበብ መንገድ መግቢያውን የቀደደለት ከጥበብ ሥራዎች ጋር የነበረው ቅርበት ነበር። ከመጽሐፍ ሻጭነት ለጉምቱ ደራሲነት የበቁ እንዳሉ ሁሉ ከፊልም አከራይነት ወደ ፊልሙ ኢንዱስትሪ የጠለቁም ብዙ ናቸው። ስንታየሁም ከእነዚህ ቪዲዮ ቤቶች ከወጡት አንዱ ነው። ታዲያ የጀመረው ያኔ ፊልም ብቻ ሳይሆን ፊልም ከነዲቪዲው በሚከራይበት ዘመን ላይ ነበር። ይህን ሲሠራና የሚያከራያቸውን ሁሉ ሲመለከት ከቆየ በኋላ ወደ ፎቶ አንሺነት ገባ። በሙያው በፍጥነት እያደገ መላው ሀገሪቱን የሚያካልል ተጓዥ ሆነ። ከተለያዩ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች እንዲሁም የውጭ ዜጎች ጋር ትስስሩን አፈጠነው። አውደ ርእዮችን በማዘጋጀት የፎቶግራፍ ሥራዎችን ለእይታ ማብቃቱን ተያያዘው።

ይህን ጊዜ የተመለከቱትም ወደ ፊልም ጥበብ መግቢያውን አመቻቹለት። በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኬኒያና ዱባይ በመሄድም በፊልም ስክሪፕት አጻጻፍና በዳይሬክቲንግ ብቁ የሚያደርጉትን ሥልጠናዎችን ወሰደ። በአፋር ክልል ውስጥ ከፈረንሳይ ሀገር ከመጡ የፊልም ባለሙያ ልዑካን ጋር በህጻናት ዙሪያ በተሠራው ዶክመንተሪ ፊልም ስንታየሁ ችሎታውን አስመሰከረ። በስክሪፕትና ዳይሬክቲንግ የሠራበት እርሱ ነበር። በ1996ዓ.ም የወጣው "ቀዝቃዛ ወላፈን" ፊልም በኢንዱስትሪው ውስጥ የማስጀመሪያ ፊሽካ ነበር። በተለይ ለስንታየሁ። አቅሙን ከፍ እያደረገና በጉልህ እየታየ የመጣውም ከዚያን በኋላ ነበር። ከሚሊኒየም ሰሞናት ጀምሮ ከምንመለከታቸው ጣፋጭ የሙዚቃ ክሊፖች ውስጥ ስሙ አይጠፋም። ከሕዳሴው ግድብ ሥራዎች ጀምሮ በልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎችም ስሙ የሚነሳ ነበር። ዛሬ ያን በጎነት ለራሱ ሽቷል።

ተሰጥኦ ልክ እንደፍሬ ዛፍ ማለት ነው። በአንድ ጀንበር ዛሬ ተክለው፣ ዛሬውኑ ኮትኩተው ፍሬውን ለመብላት የሚያሰናዱት አይደለም። ከልጅነት እስከ ዕውቀት በደም ውስጥ ተሳስሮ ዕለት ዕለት ሲያቆጠቁጥ የሚኖር እንጂ። ገጣሚው ከመግጠሙ በፊት የተገጠመውን እያነበበ ይደርሳል። ፀሐፊውም በጽሑፎች ውስጥ ያልፋል። ተዋናዩም ቢሆን ትወናን ሳያጤን አይመጣም። በእንክብሉ ሁሉም ከራሳቸው ሥራዎች ውጭ የሆነ መነሻ አላቸው። ስንታየሁ ሲሳይ የሙዚቃ ክሊፕ ዳይሬክተር እንደመሆኑ አስቀድሞ በቆንጆ ጥራት የተሠሩ የሙዚቃ ምስሎችን ተመልክቶ ተጠበበ እንዳንል፤ ያደገው ፎቶግራፍ እንኳን ብርቅ በነበረበት ዘመን ላይ ነው። ቢሆንም ግን እሱም ሊያስታውሰው የሚችለው አንድ ነገር አለ፤ እሱም ባለ ነጭና ጥቁር ምስሉ ቦርጫም ቴሌቪዥን ነው። ብቸኛው አንቴና በሆነው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚታዩ የሙዚቃ ክሊፖች ነበሩ። መልካሙ ተበጀ፣ ጥላሁን ገሠሠ፣ ዓለማየሁ እሸቴ፣ ሀመልማል አባተ፣ አስቴር አወቀ... እያለ ከሚመጣው ጀንበር ጋር ከቴሌቪዥኑ መስኮት ላይ እየተፈራረቁ ሲውረገረጉ ተመልክተናል።

ቅሉ ግን የምንመለከታቸው ከአንድ መናፈሻ ውስጥ ካለ ዛፍ ፊት ቆመው፣ ወይ ደግሞ ከአንደኛው መንገድ ዳር ጀምሮ እስኪያልቅ የምንመለከተው አንድ እነርሱኑ ብቻ ነበር። በጥቅሉ ዛሬ በአንድ የሙዚቃ ክሊፕ ውስጥ ወሳኙ ነገር የምንለው "ሎኬሽን" አልነበረውም። ቀጥሎ በነበረው የ90ዎቹ አጋማሽ "ክሊፕ" የምትለዋን ነገር እያወቅንና እየተላመድን ስንመጣ ግን ነገሮች መቀየራቸው አልቀረም። በዚያው ሰሞን ላይ ብቅ ብሎ ሙዚቃን መሳጭ ፊልም ያደረገ አንዱ ስንታየሁ ሲሳይ ነው።

ጥበብና ጥበበኛው አንድ መንገድ ላይ ተገናኙ። ከዚህ ቀደም ብሎ በዶክመንተሪ ፊልሞች ውስጥ የስንታየሁ ስም ከፍ ማለት ጀምሮ ነበር። ግን ትክክለኛው መዳረሻው ሙዚቃው መሆኑን በማመን ወደዚያው ከሚወስደው ባቡር ውስጥ ገብቶ ተሳፈረ። ከመንደሩም ደረሰ። የአንደኛውን ጓደኛውን ትከሻ ተደግፎ የሙዚቃው ግንብ ላይ ወጣ። አጥሩን ዘሎም ወደ ግቢው ገባ። "ባቡሬ" የበኩር የሙዚቃ ሥራው ነበር። ድምጻዊ ታደለ ሮባ ዋና ካፒቴን፣ ጋሽ አበራ ሞላ በረዳትነት ከድሬዳዋ አዲስ አበባ በሚያከንፏት የሙዚቃ ባቡር ስንታየሁ ተጠበበበት። ሙዚቃው በድምጽ ራሱን ችሎ የሚደመጥ ቢሆንም ወደ ክሊፕ መቀየር ግን እስካሁን ከነበረው ሂደት የባሰ ፈታኝ ነው።

ጆሮ ሞኝ ነው በጥቂት አሞኝተው ለመሸወድ ይቻላል፤ ዓይን ግን አድበስብሰው በዋዛ ሊያመልጡት አይቻልም። ለዓይን ሳቢ፣ ለልብ የሚጣፍጥ አድርገው ለመሥራት ካልቻሉ ሙዚቃውን ከነድምጹ ይዞት ገደል ይገባል። በድምጽ ወደናቸው ደጋግመን ስንሰማቸው በክሊፕ ሠራን ተብሎ የጠበቅነውን ውበት በማጣት የሰለቸናቸው ሙዚቃዎች ስለመኖራቸውም ልብ ይሏል። የክሊፕ ባለሙያ ቀድሞ በድምጽ ደረጃ እንደሠራው ባለሙያ እንዳሻው በተመቸው ዓይነት አድርጎ የመሥራት ነፃነት የለውም። ከምስሉ ጋር የሚጣጣም እንዲሆን ድምጹን ወደ ምስሉ ሊያመጣው አይችልም። ያለው አማራጭ ምስሉን ወደ ድምጹ በመውሰድ፣ ለድምጹ የሚሆነውን ምስል መፍጠር ብቻ ነው። ስንታየሁም ይህን ለማምጣት ለ"ባቡሬ" ልክ እንደፊልም ሁሉ ስክሪፕት ጽፎ፣ ከጅምር እስከ ፍጻሜ እያንዳንዷን ቦታ መርጦ፣ አልባሳቱን ጨምሮ እያንዳንዱን ጥቃቅን ሁሉ አሰባጥሮ "ባቡሬ"ን ሠራው። ባቡሩም እየገሰገሰ መጣ። ስንታየሁ ገና በመጀመሪያው ሥራው አድናቆትና ተወዳጅነትን አተረፈ። ሁለተኛውን በምናሉሽ ረታ ሱዳንኛ ቀጠለ።

ከዚህ በኋላማ ምኑ ተነግሮ ያልቅና ባቡር ተፈተለከ። በነፃነት መለሰ "የታል ልጁ የታል" መባል ተጀመረ። አንድ ሰሞን ላይ ሳር ቅጠሉ ሁሉ ሰለል! ኩቡል! ሲሉበት በነበረው በሳሮን ተፈሪ "ሚሶ ነጋያ" ስንታየሁ እጁን ለመሳም በቅቶበታል። የሐመሮችን ውበት ከነሀረጉ መዞ በዓይን የሚበላ፣ በጆሮ የሚመጠጣ ሙዚቃ አድርጎታል። ከትምህርት ቤት እስከ ፍቅርና የትዝታ ዳገት ከወላይታ ባሕል ጋር ቋጭቶ ያቀረበው የጥበቡ ወርቅዬ "ሊጋባ"ን ማን ይረሳል። ሄለን በርሄ በ"ልቤ"፣ ዘለቀ ገሠሠ ደግሞ "ሀገሬን"፣ ኤደን ገ/ሥላሴ "ሰው ዋኖ"ን ጨምሮ እስከ ሀመልማል አባተ፣ ኃይልዬ ታደሰ ኧረ ምኑ ቅጡ። የእርሱ የጥበብ ዓይኖችና እጆች ያልደረሱበት የሙዚቃ ክሊፕ የለም።

ሌት ተቀን፣ ነግቶ ሲመሽ ውሎና አዳሩ ሙዚቃው ላይ ሆነ። ራሱን ዘንግቶ እረፍት አልባ ሆነባቸው። "... እንዲያውም ብዙ ሽበት የመጣው ሥራዎቼ በጣም ያስጨንቁኝ ስለነበረ ነው" በማለት በቀልድ ሳይሆን ምሽት ጭምር እያነጋ ይሠራ እንደነበረ ያወሳል። ሰው ሥራውን ይገልጽ ይሆናል፣ ሥራ ሰውን ሲገልጽ ግን ስንታየሁ ሲሳይን ነው። ስል ቃላትን ለማደማመቅ አይደለም። የእርሱ ሥራዎች የራሳቸው የሆነ ቀለም አላቸው። ጠረናቸው የስንታየሁ መልካቸው ስንታየሁን ነው። የሙዚቃ ክሊፖቹን ምስል ስንመለከት ገና የማን እንደሆኑ ለይተን እናውቃቸዋለን።

እነዚህ ታላላቅ የሙዚቃ ምሰሶዎችን በማቆም ድፍን 20 ዓመታትን ያስቆጠረው ስንታየሁ ሲሳይ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ በኑሮው ሞቆት ባይደላውም፣ ከፍቶት ግን አንገት አልደፋም ነበር። ቢመችም ባይመችም እንደማንም ያለሰቀቀን ኑሮና ቤተሰቡን ሲመራ ቆይቶ ነበር። በመሃል ግን የዛሬ አምስት ዓመታት ገደማ ድንገት ከሙዚቃ እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። አንገቱን ደፍቶ በኑሮ በረሀ ላይ ሲናውዝ፣ የመከራ ሀሩር የቤትና ልጆቹን እናት ሲያነድ "ምነው ወዳጄ?" ባይ አጣ መሰል ሥራው ሳይታይ፣ ድምጹም ሳይሰማ ቀረ። ሥራ ሥራውን ሲል ከጎን ኑሮ ሽመሉን መዘዘለት። ስንታየሁ ያቺን የእሳት ዳር ፍሬ ወደመሆን የገባው ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ነበር።

ፊቷን አዙራ የጠለቀች ጀንበር ጨለማውን እንዳስታቀፈችው ሳትመለስ ቀረች። የሕይወት ግርፋት፣ የኑሮ እሳት ተቀጣጠለ። ከነበረባት የከፍታ አንጓ ላይ ረግፎ፣ ሲምዘገዘግ ቁልቁል ወርዶ ከወላፈኑ ፊት ጠብ! አለ። እነዚያ ዓመታት ለእርሱ የጨለማ ዘመናት ነበሩ። በደህናው ጊዜ ያካበተው ሀብት ንብረት የለምና ዙሪያው ያሉትን ቤተሰቦቹን ለማኖር ሲል ሲሠራባቸው የነበሩትን ቁሳቁሶች አንድ ሁለት እያለ ሸጣቸው። ለረዥም ዓመታት በግል መኪናው መንቀሳቀስን የለመደው ስንታየሁ እሷንም ሸጣትና የታክሲና የባሱን ግፊያ ተቀላቀለ። በዚህ ሁሉ መስዋዕትነት ለልጆቹ ትምህርት ቤት፣ ለቤተሰቡ እያለ ላለመውደቅ ሲፍጨረጨር ቆይቶ በስተመጨረሻ ነበልባሉ ከፋ። እያደር ህመሙ ጠና። ሁሉም ነገር ከፋ። "...የቤት ኪራይ ለመክፈል አቅቶኝ ፖሊስ እስኪከሰኝ፣ ልጆቼ ደጅ ወጥተው እስኪያለቅሱ ድረስ... የልጆቼን የትምህርት ቤት ክፍያ ለመክፈል አቃተኝ። በኔ ልጆች የደረሰ በማንም ልጅ አይድረስ..." ሲል በተሰበረ ልብ፣ እየተንገሸገሸ የመከፋቱን ጥግ ገልጾ ነበር።

ከእሳት ዳር የነበረው ስንታየሁ ሲሳይ ከመሞት መሰንበት ሲል ከሚዲያ አደባባይ ከወጣ በኋላ እንደመረሳቱ በዝምታ አልታለፈም። "አለሁልህ!" ሲል በቻለው ሁሉ ጎኑ የቆመ ቀላል ሰው አይደለም። በየማህበራዊ ሚዲያውና በተለያዩ መንገዶች 3 ሚሊዮን ያህል ብር ተሰበሰበለት። እሳቱ እየረገበና ፍሬውም በተስፋ የለመለመ መሰለ። በዚህ መሃል ጉዳይህ ጉዳዬ ብሎ እየተንቀሳቀሰ ያለ አንድ ኮሚቴም ይገኛል። አርቲስት ስለሺ ደምሴ(ጋሽ አበራ ሞላ)፣ አርቲስት ተስፋ ብርሃኔ፣ ፎቶግራፈር አንቶኒዮ፣ ደረጀ ምክሩ እንዲሁም ጋዜጠኛ መሰለ ገብረ ህይወት እና አብረሃም ግዛው የተዋቀሩበት ኮሚቴ ነው። ከሳምንት በፊትም ለጋዜጠኞች ጥሪ አድርገው ነበር። በሰጡት መግለጫ ውስጥም "...እስካሁን የተደረገለት ድጋፍ እንዳለ ሆኖ፤ ወደ ሥራው እንዲመለስ በማድረግ እርሱን በቋሚነት ስለማቋቋም አስበናል..." በማለት ሃሳቦች ተንሸራሽረዋል። የሠራላቸውን ድምጻውያን በማሰባሰብ ኮንሰርት የማዘጋጀቱን ነገርም እያሰላሰሉበት ነው። ትልቁ ጋሬጣ የሆነበትን የመኖሪያ ቤት ችግሩን ለመቅረፍም ከንቲባው ጽህፈት ቤት ድረስ ገብቶ ለማሳማን እንደሚተጋ ኮሚቴው አሳውቋል። የልጆቹንም የትምህርት ቤት ጉዳይ ቢሆን ትምህርት ቤቱ በኛ ጣለው ብሎታል። ከእንግዲህም የወንዝ ዳር እንጂ የእሳት ዳር ፍሬ እንደማይሆን ተስፋ እናድርግ። ሁሉም መልካም ይሆናል!

## ዜና



# በበጋ የስንዴ መስኖ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እየተደረገ ነው ብለዋል።

በበጋ ወቅት ሁለት ነገሮችን ለማልማት ማለትም የአትክልት፣ የፍራፍሬና የስንዴ ምርቶችን በማልማት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በበልግ፣ በመኸር፤ በበጋ በሶስት ወቅቶች የግብርና ምርቶችን በማምረት ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ በተሠራውም ሥራ ትልቅ ውጤት እየተገኘ ነው፤ በ2017 ዓ.ም የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ለማግኘት የታቀደውን 172 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እውን ለማድረግ ለአርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያ ግብዓት ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ከበጋ መስኖ ልማት የሚጠበቀውን የስንዴ፤ የአትክልትና የፍራፍሬ ምርትን ለማግኘት ለአምራቹ ማህበረሰብ ሞተሮችን፣ ፓንፖችንና ለመስኖ ልማት የሚያገለግሉ ትልቅና ጉልበት ያላቸውን ሞተሮች በመግዛት በድጋፍ መልኩ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በ2017 ዓ.ም የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በሁሉም ክልሎች በስፋት እየተሠራ ቢሆንም በተለይ በኦሮሚያ ክልል በይበልጥ ለማልማት እየተሠራ ነው፤ በክልሉ የበጋ ስንዴ ልማት ለማልማት እየተሠራ ባለውም ሥራ እስካሁን ማለትም ከጥቅምት 19/2017 ዓ.ም ድረስ በባህላዊ መንገድ ስድስት መቶ 70 ሺህ ሄክታር መሬት፣ በኮባይነር አንድ መቶ 80 ሺህ ሄክታር በአጠቃላይ ስምንት መቶ 50 ሺህ ሄክታር መሬትን ለዘር የማዘጋጀት ሥራ ተሠርቷል፤ ለዘር ከተዘጋጀውም ከስምንት መቶ 50 ሺህ ሄክታር መሬት ውስጥ አምስት ሺህ 113 ሄክታር መሬት የሚሆነው በዘር ተሸፍኗል ሲሉ አብራርተዋል።

አርሶ አደሩ ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እያገኘ ያለውን ጥቅም በመገንዘብ በግሉ ሞተሮችን፣ ፓንፖችን እየገዛ ጥቅም ላይ እያዋለ ነው፤ ምርትና ምርታማነቱንም እያሳደገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ለማግኘት የታሰበውን ምርት ተግባራዊ ለማድረግ ልማቱን በቴክኖሎጂ የማስደገፍ፣ ምርጥ ዘር የማቅረብ፤ በልማቱ ላይ የግሪሳ ወፍና አንበጣ ተከስቶ እቅዱ እንዳይኮላሽ ለመከላከል የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ከተከሰተም ለመከላከል አምስት የርጭት አውሮፕላኖቻቸውና መኪናዎች ዝግጁ ናቸው ያሉት አቶ ከበደ፤ ለሰብሉ አስፈላጊውን ጥበቃና ቁጥጥር የማድረግ ሥራም የሚሠራ ይሆናል ሲሉ ጠቁመዋል።

ተግባራዊ የተደረገውን የሀገር በቀል ኢኮኖሚው ማሻሻያን ውጤታማ ለማድረግ ግብርናው ትልቅ ሚና ይጠበቅበታል፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የሚጠበቅበትን ሚና እየተጫወተ ይገኛል ብለዋል።

# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቀፍና ክልላዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሶስቱ መንግሥት አካላት ተወካዮች፣ የተለያዩ ማህበራትና ተቋማት ተወካዮችና እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ ምሁራንና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ዋነኛ ተሳታፊዎች እንደሚሆኑ ኮሚሽነር ሙሉጌታ ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሐረር፣ በአፋር፣ በሱማሌ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራውን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን መቻሉን ኮሚሽነሩ አስታውቋል

ኮሚሽነር ዘገየ አስፋው በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ኮሚሽኑ በአዋጅ በተሰጠው ሃላፊነት መሠረት በሁሉም ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች እየሠራ ይገኛል። በአማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ኮሚሽኑ ሥራዎችን የጀመረ ቢሆንም፤ ይህን ለማስቀጠል የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡

በዚህም በአማራ ክልል የአስተባባሪዎች ልየታ ተደርጎ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ በተጠቃለለ ሁኔታ ከወረዳ ጀምሮ የአስባባሪዎች ስልጠና እንደሚሰጥና ከዚያም በመቀጠል የተሳታፊዎች ልየታ እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

በትግራይ ክልልም ንግግሮች የተጀመሩ ሲሆን ለምክክሩ ፍቃደኝነት እንዳለ ማወቅ እንደተቻለና በቀጣይም የምክክሩ ሂደት የሚጀመር ይሆናል ሲሉ ኮሚሽነር ዘገየ አመላክቷል።

በዛሬው እለት በሚጀመረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ተሳታፊዎች ምክክሩ የሚኖረውን ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳ በመረዳት በምክክሩ በንቃት እንዲሳተፉም ጥሪ ቀርቧል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ ዩክሬንን ድል እስከምታደርግበት ቀን ድረስ ድጋፏን እንደምትቀጥል ሰሜን ኮሪያ አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሰሜን ኮሪያ ሩሲያ ከዩክሬኑን ጋር የጀመረችውን ጦርነት እስከምታሸንፍ ድረስ እንደምትደግፋት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ገለጹ፡፡ የሰሜን ኮሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቾ ሰን ሁይ ከሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ ጋር በሞስኮ ትናንት ውይይት አድርገዋል።

የሰሜን ኮሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቾ ሰን ሁይ በውይይቱ ላይ እንደገለጹት፣ ሰሜን ኮሪያ ሩሲያ በዩክሬን እያካሄደች ያለውን ጦርነት እስከምታሸንፍ ድረስ እንደምትደግፋት መግለጻቸው ተነግሯል፡፡

"ታሪካዊው እና ባህላዊው ግንኙነታችን ወደማይገበር ወታደራዊ ጓድነት አድጓል" ያሉት ቾይ፣ በፑቲን "ብልህ አመራር" የሩሲያ ጦርና ሕዝብ "የሉዓላዊነት ዘመቻቸውንና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያደርጉትን ቅዱስ ትግል ድል ያደርጋሉ።" በማለት "እኛም ድሉ እውን እስከሚሆንበት ቀን ድረስ ከሩሲያ ጓዶቻችን ጎን እንደምንቆም እናረጋግጣለን" ብለዋል።

የሁለቱ ሀገራት መሪዎች ባለፈው ሰኔ ወር በፒዮንግያንግ የፈረሙትን ወታደራዊ ስምምነት የበለጠ ማጠናከር እንዳለባቸው መግለጻቸውንም ተነግሯል፡፡

የሩሲያው አቻቸው ላቭሮቭ በበኩላቸው፣ ምዕራባውን ኔቶን ወደ ምስራቅ ማስፋፋታቸውን እና ዘረኛው ሥርዓት የሩሲያ የሆነን ሁሉ እንዲያጠፋ ማበረታታቸውን ተከትሎ የኮሪያ ወዳጆቻችን ለወሰዱት በመርህ ላይ የተመሠረተ አቋም ምስጋና እናቀርባለን ሲሉ መናገራቸው ተገልጿል፡፡

በሁለቱ ሀገራት ጦር መካከል ቅርብ ግንኙነት መኖሩንና ይህም ወሳኝ የደህንነት ሥራዎችን ለመከወን እንደሚያስችላቸው ላቭሮቭ ገልጸዋል፡፡

ላቭሮቭም ሆኑ ቾይ፣ አሜሪካ፣ ኔቶ እና ደቡብ ኮሪያ፣ በዚህ ሳምንት ሰሜን ኮሪያ ወደ ሩሲያ 10ሺ ወታደሮችን ልካለች በማለት ያወጡትን መግለጫ አልጠቀሱም። የክሬሚሊን ቃል አቀባይ ዲሜትሪ ፔስኮቭ ለእንደነዚህ አይነት መግለጫዎች" ከዚህ በፊት ከተባለው በላይ የሚጨመር የለም" ብለዋል።

ሆኖም ግን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከእነዚህ ውስጥ 8ሺ የሚሆኑት ወታደሮች የዩክሬን ወታደሮች ባለፈው ነሐሴ ወር የሩሲያን ድንበር ጥሰው ወደገቡበት ኩርስክ ግዛት መድረሳቸውን ገልጸዋል።



## የእስራኤል ወታደራዊ መሪዎች በጋዛና በሊባኖስ የተሰጣቸውን ዓላማ በሙሉ ማሳካታቸውን አስታወቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እስራኤል ወታደራዊ መሪዎች ሀገሪቱ በጋዛና ሊባኖስ በወታደራዊ ዘመቻዎች ማከናወን የፈለገቻቸውን ዓላማዎች በሙሉ ማሳካቷን አመልከተዋል፡፡ እስራኤል በወታደራዊ ኃይል የምትችለውን ሁሉ እንዳሳካች የገለጹት አዛዦቹ፣ ፖለቲከኞች ስምምነት ላይ ለመድረስ ጊዜው አሁን መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የእስራኤል ጦር ከፍተኛ ጄነራል ከሰሞኑ በሰሜናዊ ጋዛ ከሚገኙ መኮንኖች ጋር ወቅታዊ የጦርነቱን ሁኔታ ለመገምገም በነበራቸው ስብሰባ፤ የግጭቱ ከዚህ በኋላ መቆየት እምብዛም ጥቅም የለውም ማለታቸው ተገልጿል፡፡

የሀገሪቱ ኢታማዦር ሹም ሄርዚ ሄልቪ እንደተናገሩት፣ “በጋዛ የሰሜን ጋዛ ብርጌድ አዛዥን ብንገድል ለቡድኑ ሌላ ውድቀት ነው፤ ነገ ምን እንደሚገጥመን አላውቅም። ነገር ግን ይህ ጫና ወደ ተጨማሪ ስኬቶች እንድንቀርብ ያደርገናል” ማለታቸው ተገልጿል፡፡

በሊባኖስ ሄዝቦላህ ላይ እየተካሄደ በሚገኘው ጦርነት አሁን በሚገኝበት ደረጃ አንድ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ እድሉ አለ ሲሉ ኢታማዦር ሹሙ መግለጻቸው ተዘግቧል፡፡

የመከላከያ ሚኒስትራቸው ዮአቭ ጋላንት “በጋዛ ፍፁም ድል የሚለው ሃሳብ ከንቱ ነው” ሲሉ በነሀሴ ወር ከፓርላማው ቋሚ ኮሚቴ ጋር በዝግ በተደረገ ስብሰባ መናገራቸው ተሰምቷል፡፡

ሚኒስትሩ ከሰሞኑ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባቀረቡት ሪፖርትም “የተሻሻሉ የዘመቻ ግቦች በሌሉበት ባልጠራ ኮምፓስ እያደረግን ያለነው ውግያ የዘመቻውን ውጤት ይጎዳል” ማለታቸውም ተዘግቧል፡፡

በተጨማሪም አሁን ላይ ትኩረት መደረግ የሚገባው በጋዛ የቀሩትን ታጋቾች ማስለቀቅ መሆኑን በመግለጽ፣ ከሃማስ ምንም አይነት ወታደራዊ ስጋት አለመኖሩን ማረጋገጥና የሲቪል አገዛዝን ተግባራዊ ማድረግ ሊሆን እንደሚገባ ተናግረዋል።

በጋዛ “ፍፁም ድል” ለማስመዝገብ ደጋግመው ቃል የገቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ ይህን ሃሳብ ለመቀበል የሚቸገሩ ይመስላል፡፡


# ስፖርት





# ‹‹ጎራዴው›› - የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቁጭት!

**ቦጋለ አበበ**



አሠልጣኝአስራት ኃይሌ

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በአሠልጣኝነት ገናና ስም ካላቸው ጥቂቶች አንዱ አስራት ኃይሌ ስለመሆኑ በርካቶች ይስማማሉ። የእግር ኳስ ቤተሰቡ "ጎራዴው" በሚል ቅፅል ስም የሚያውቀው አሠልጣኝ አስራት ኃይሌ ከበርካታ ታላላቅ የኢትዮጵያ ክለቦች እስከ ብሔራዊ ቡድን በዘለቀ የአሠልጣኝነት ሕይወቱ "አንቱ" ያስባለውን ሙያዊ አበርክቶ በውጤታማነቱ አስመስክሯል።

ይህ የእግር ኳስ ባለውለታ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ባበረከቱት ልክ ባይዘመርለትም። ያለውን ትልቅ አቅም በተለይም በእድሜው የመጨረሻ ዓመታት የኢትዮጵያ እግር ኳስ አንጠፍጥፎ አለመጠቀሙ የብዙዎች ቁጭት ቢሆንም ሥራው ከመቃብር በላይ ህያው ሆኖ በትውልዶች ሲታወስ ይኖራል።

አስራት ከተጫዋችነት እስከ አሠልጣኝነት የዘለቀው የረጅም ዓመት የእግር ኳስ ሕይወት በሰፈር ውስጥ መስከረም ኮከብ የተባለ ቡድን እንደተጀመረ በሕይወት ታሪኩ ላይ ሰፍሮ ይገኛል። በ1953 ዓ.ም በዳርማር ህጻናት ከተጫወተ በኋላ ችሎታውንና ለስፖርት ያላቸውን ፍቅር በማየት በወቅቱ የድሬዳዋ ጥጥ ማህበር ወይንም ኮተን አሠልጣኝ የነበረው ታሪካዊው ሉቻኖ ቫሳሎ በ1963 ክለቡን እንዲቀላቀል አድርጎታል። በኮተን ቆይታው ባሳየው ብቃትም ለሐረርጌ ምርጥና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለመመረጥ አስችሎታል። በኮተን ቆይታው ሁለት ጊዜ የኢትዮጵያ ክለቦች ቻምፒዮና ፤ የሀረርጌ ክፍለ ሀገር ምርጥ ቡድን ጋር አንድ ዋንጫ አንስቷል።

1968 ዓ.ም አስራት ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ የመጣበት ነበር። ለ 3 ዓመት በተጫዋችነት እንዲሁም በአምበልነት ቆይታ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም ለዋናው ብሄራዊ ቡድን በመመረጥ ለ 9 ዓመታት የተጫወተ ሲሆን፣ በ 1968 ዓ.ም በኢትዮጵያ አዘጋጅነት በተደረገው የአፍሪካ ዋንጫ 4ኛ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ አስተዋፅኦ ነበረው።

ከዚህ በኋላ ፊቱን ወደ አሠልጣኝነት ያዞረው ጎራዴው በመጀመሪያ ለትግል ፍሬ ቡድን በአሠልጣኝ ተጫዋችነት በ 1972 ዓ.ም የአዲስ አበባ አንደኛ ዲቪዚዮን ቻምፒዮን እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመቀጠል ለህንፃ ኮንስትራክሽን 50 ክለቦች በአዲስ ሲዋቀሩ ጥሩ 10 ክለቦች ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ሲያልፉ ክለቡን አራተኛ ደረጃ እንዲይዝ በማድረግ ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ማሳደግ ችሏል።

የአሠልጣኝነት ችሎታውን በማጎልበት በተጫዋችነት ያገለገለውን ቅዱስ ጊዮርጊስን ከ 1983-1992 ዓ.ም ያሠለጠኑ ሲሆን በቆይታውም የተለያዩ ዋንጫዎችን አሳክቷል። በ1975 ዓ.ም ቡድኑ ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ከማሳደግ ጀምሮ በ1987 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቻምፒዮና የጥሎ ማለፍ ዋንጫ፤ የአሸናፊዎች አሸናፊ ዋንጫ ፤ የፀባይ ዋንጫ ጠራርጎ በማሸነፍ ኮከብ አሠልጣኝ ሲሆን ከክለቡም ኮከብ ተጫዋች አስመርጧል።

የቀድሞው የመስከረም ኮከብ፣ ዳርማር፣ ድሬዳዋ ጥጥ ማህበር፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ትግል ፍሬና ለሌሎች ክለቦች ድንቅ የተከላካይ ቦታ ተጫዋች ወደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝነት የመጣው የተስፋ ቡድን አሠጣልጣኝ በመሆን ነበር። ቀጥሎም የዋናው ብሄራዊ ቡድን አሠልጣኝ በመሆን በኢትዮጵያ በተደረገው የሴካፋ ውድድር ላይ ዋንጫ በማንሳት ብቸኛ የሆነበትን ታሪክ አኑሯል።

ከቅዱስ ጊዮርጊስ በተጨማሪ በክለብ አሠልጣኝነት ሕይወቱም በመከላከያ የጥሎ ማለፍ ዋንጫ፤ በሙብራት ሃይል ሲቲ ካፕ ዋንጫ ያሳካ ሲሆን የኢትዮጵያ መድህን ከአንደኛ ዲቪዚዮን ወደ ፕሪሚየር ሊግ አሳድጓል።

በመጨረሻም በደደቢት ስፖርት ክለብ ከአማካሪነት እስከ አሠልጣኝነት በነበረው ቆይታ በፕሪሚየርሊጉ ዋናው በሁለተኛ ደረጃ እንዲያጠናቅቅ አድርጓል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ አሠልጣኞች ማህበር መሥራችና አባል በመሆን፤ የአዲስ አበባ እግር ኳስ አሠልጣኞች ማህበር ፕሬዚዳንት፤ የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግሏል፡፡ በአጠቃላይ በአሠልጣኝነት ሕይወት ዘመኑ ከ 30 በላይ ዋንጫዎችን ማሳካትም ችሏል፡፡ ልምድና ሙያውን ያለ ስስት አጋርቷል፤ በርካታ ተተኪዎችን ፈጥሯል፤ በመገናኛ ብዙሃን በጨዋታ ትንታኔ ሙያዊ እውቀቱን አካፍሏል።

ሃይለኛ፣ ደፋር፣ ቀጥተኛ፣ አልሸነፍ ባይ፣ እጅ የማይሰጥ፣ የሰላ፣ ስኬታማ በመሆኑ "ጎራዴው" የሚል ቅፅል ስም የተሰጠው አሠልጣኝ አስራት ኃይሌ ለረጅም ጊዜ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በህክምና ሲረዳ ቆይቶ ጥቅምት 15 ቀን 2017 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ እንዲሁም በርካታ የስፖርት ቤተሰቦች በተገኙበት ልክ የዛሬ ሳምንት በጴጥሮስ ወጳውሎስ ሥርዓተ ቀብሩ ተፈፅሟል፡፡


## ግልፅ ጨረታ ማስታዎቂያ

## የግዥ መለያ ቁጥር MOR JBO-001/2017

በገቢዎች ሚኒስቴር የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለ2017 በጀት ዓመት የሆቴል አገልግሎት ግዥ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለፁትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተጫራቾች ቀርበው መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. በሆቴል ዘርፍ የተሰማሩበት በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው፣የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ የሆነ እና በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት እና የኮከብ ደረጃ የተሰጠ ማስረጃ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል እንዲሁም ለጅማ ባለ 3 ኮከብ እና በላይ፣አሶሳ፣ጋምቤላ እና ሚዛን የኮከብ መስፈርት ግዴታ አይደለም፣የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያለው፣የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና(ቢድ ቦንድ)ጠቅላላ የምላችሁትን የአገልግሎት ዋጋ 0.5% እስከ 2% በማስላት በባንክ ክፍያ ማስያዥያ (CPO) ወይም በጥሬ ገንዘብ በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ስም ማስያዝ የሚችል፣
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በማይመለስ ብር 200.00(ሁለት መቶ ብር)ብቻ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15(አስራ አምስት) የስራ ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2፡00-6፡00 እና ከሰዓት 7፡00-11፡00 እንዲሁም ቅዳሜ ጠዋት ከ2፡00-6፡00 ሰዓት በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅ/ጽ/ቤት መርካቶ አዋሽ ባንክ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ድረስ በመምጣት መግዛት ይችላሉ፡፡
4. የአገልግሎት ዝርዝር መግለጫ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በጨረታ ሰነዱ ላይ በጥንቃቄ በመሙላት በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ፊርማና የድርጅቱ ማህተም በመምታት በታሸገ ኢንቨሎፕ ቴክኒካሉን እና ፋይናንሽያሉን ዋናው እና ኮፒው ለየብቻ በኢንቨሎፕ ወይም ካኪ ፖስታ በማሸግ በቅ/ጽ/ቤቱ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት የሚችሉ፣
6. ጨረታው የሚዘጋበትና የሚከፈትበት ሰዓት ከጨረታ ሰነድ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የጨረታ ሰነድ መቀየር፣ማሻሻል ወይም ከጨረታው ራስን ማግለል አይቻልም፡፡
8. የተሰረዘና የተደለዘ፣የተፋፋቀ እንዲሁም በግልፅ የማይነበብ የጨረታ ዋጋ ተቀባይነት አይኖረውም፣
9. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
10. ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 047-111-56-00/047-211-04-43 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**በገቢዎች ሚኒስቴር የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**



## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍባለሙብት እነ ወ/ሮ ሔለን ጌታቸው እና በፍ/ባለዕዳ እነ ወ/ሮ ራሔል እጀታ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 261800 በ28/3/2014 ዓ.ም እና መ/ቁ 95544 በ3/8/2014 በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአዲስ ከተማ/ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቤ.ቁ 270 የሆነውን መኖሪያ ቤት እና መጋዘን በካርታ ቁጥር 27721 በእጀታ ወርዶፋ ስም ተመዝግቦ የሚገኝና የቦታው ስፋት 451 ካ/ሜ ቤት የይዞታው አዋሳኞች በምዕራብ 272፡273 እና 274 በምስራቅ 264 እና 265 በስተደቡብ 267 እና በስተሰሜን መንገድ የሚያዋስነው ቤት የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 21,060,026(ሃያ አንድ ሚሊዬን ስልሳ ሺ ሀያ ስድሰት ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ህዳር 25 ቀን 2017 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለሙብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለሙብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4ኛውን በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**